
# እምቢ በሉ

ሰዎች



# እምቢ በሉ

ሰዎች

የጸሬሲው፡ መብት፡ የተጠበቀ፡ነው።

# እምቢ በሉ

## ሰዎች

ከዳኛቸው ፡ ወርቁ ፡

አዲስ ፡ አበባ ፡ ፲፱፻፷፯ ዓ.ም.

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ታተመ

# መታሰቢያነቱ

ለታከለ፡ ወልደ፡ሐዋርያት፡(ደጃዝማች)

ቍ.ም፡ጸሐፌ፡ዘውዱ፡ተፈራ።

የካቲት — ፲፱፻፷፯ ዓ.ም.

እንደ መግቢያ።

ሀሁህ
ለትኖዴዴ።
አትባክን ውሰህ።
ትቱቲ።
ንፍሮህን ቃትመህ።
ዘባተሎህን ደርበህ።
ችቹቺ።
አዛባና ሽንት።
ከመሬት፡
የተኛህበትን አጎዛ፡
ዘልቆ ስታገኘው።
ወገብህን ስትመቻቺ።
ክኩኪ።
ሹክ የወጋህን።
ድንጋይ የመታህን።
እየተመለካከትክ።

ቁማልና፡ትኳን።
የጋጠውን፡አከባትህን።
አየዲባበስክ፤
ጀጂጂ።
መልከኛውና፡ጎታው።
ጺሐሬውና፡ዲኛው።
ማዩ፡ለማደ፡ተፋጠ።
ያጎዲጎኸውን።
የወሰዱኸውን።
ሲቀማህ፡ሲተያዩ፤
ኘኘኚ
በሆነ፡ባልሆነው።
በየጊዜው።
አትጎተት፤አትታሠር።
የምትመካበት፡ሕግ።
ሲጠሩ።
የምትሰው፡ኦሰኝ፤
ርርር።
ሀብትህን፡ተገፈህ።
መኖር፡አስጠልቶህ።

አ

ጦርህን፡ከጣራ፡
ጨኹርጠህ፤
ጪካ፡ቤቱ፡ገብስህ፡
ስትዞር፡
ካገር፡አገር፤
ሙውው፡
መንከራተት፡ሰልችቶህ፡
ሕይወት፡አንገፍግፎህ፡
መረት፡መሬት፡
ለለመልከቶህ፤
ሲስብህ፡
እናት፡አባትህ፡
የረገፉበት፡
አጽመ፡ርስትህ፡
ትዝታው፤
እፍ፡የሌለህ፡እንት፡ዋቶ፡አዴር፡
ሊሰማህ፡ይሆን —— ያ፡
አትል፡የምሰማህ፡
ያውቃል፡እዝጊያብሔር ?

ነሐሴ — ፲፱፻፸፫ ዓ.ም.

እንክትክት ሽርክትክት ።
ዱ ክምክም አድርጉ -
ሆድ እያስቆረጠ ።
አንጀት ስቦ ስቦ ።
ገንዘብ እንደሆነ —
ከእንስሶቹ ሌሎቶ ሰውን ያጉላው ።
ቢወዷም ቢጠሳም —
አመጣበት አገር እንመልሰው ።
ባይተዋር ነውና ለሰው ለቀየው ።

መስከረም — ፲፱፻፸፬ ዓ.ም.

አንጎራጉሬ እባክሽ ።
ወንዱን ቢነሽጠው ።
ሽለሳማ ቀርቷል ።
ፉከራማ ቀርቷል ።
ቢነካካው ድንገት ።
ምኒልካት ቢያስቾጤው ።

መስከረም — ፲፱፻፸፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡

## አኖኪ ፡ ነትራኪ ፡

አኖኪ ፡ ቀዥቃዣ ፡
ያስለፍልፍ ፡ ቀመስ -
ነቶራኪ ፡ ክልፍልፍ ፡
ሁሉን ፡ አጣጢስ ፡
ዘሳሰም ፡ ይኖራል ፡
ነገር ፡ ሲያጣቁስ ፤
ባልተጠየቀበት ፡ ባልተጠራበት ፡
ሲያወሳ ፡ ይገኛል ፡
ፈጥሮ ፡ በድንገት ፤
አያድርስ ፡ እንጂ ፡ ነው ፡
እንዲህ ፡ ያለ ፡ ሰው ፡
አያገባው ፡ ገብቶ ፡ ነገር ፡ ሲነዝረው ፤
ነዘረው ፡ ሲነዝረው ፡
እየው ፡ ተመልከት ፡
ሲተረትር ፡ አፉን ፡ ሲያጣለት ፡ ለከት ፤
አፉ ፡ ጠላቱ ፡ ነው ፡

ቋሮው፡መርዝ፡አቃሬ፡
ያልተጠራበትን፡
እልኩ፡አለን፡አፋሬ፤
ይሞራል፡ዘሳሰም፡
ነገርን፡ሲገምድ፡
ሰውን፡ሲያቆራርጥ፡
ሲቆፍር፡ጉድጓድ፤
ያንቀጠቀጠዋል፡ያሳብጸዋል፡
ትናግሮ፡እስኪያዋጋ፡
ባልሆነ፡በደል፤
ጆሮ፡ግንድ፡ወሰኑ፡
አዝሞ፡ያልገታው፡
መጥኔ፡መጥኔ፡መጥኔ፡
ብርታቱን፡ይስጠው፤
የአምባ፡ገነን፡ጀግና፡
የሚታወቀው፡
ካባይ፡ገነን፡ሰው፡ሲል፡
ጊዜ፡ባልሻረው፡
በትጥረከረከ፡በወሬ፡ዜናው፡
በማቆካለፍ፡ነው፡

ባይሠሩ ፡ ለሠራው ፤
እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ሰው ፡
ሌባዊ ፡ እምብልጥ ፡
ምኅስ ፡ ጁራፍ ፡ ነው ፡
እንዝርታዊ ፡ ቲጥ ፤
ስቀው ፡ ሲያስቁበት ፡ ሲሳለቁበት ፡
ውዳሴ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ይገኛል ፡ ሲስት ፤
መወሸከት ፡ መቅበጥበጥ ፡
በሰው ፡ ላይ ፡ መንቻረር ፡
መከነፍነፍ ፡ መናወዝ ፡
ሁሉን ፡ ማደናገር ፡
የገጡን ፡ የቆጡን ፡ ሁሌ ፡ መተባጠር ፡
ዝም ፡ የማይል ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡
ታዲያ ፡ እንደምን ፡ ይቻል ፡
እንደምንስ ፡ ይኑር — ?
እንዴት ፡ ያለ ፡ ኑሮ ፡ ነው ፡
እንዴት ፡ ያለ ፡ ሙያ ፡
ኧረ ፡ ወዲያ ፡ ወዲያ ፡
ኤዲያ ፡ ኤዲያ ፡ ኤዲያ ፡
ያለ ፡ የሌለውን ፡ የማይኖረውን ፡

ማውራት፡ማውራት፡ማውራት፡
መጥኔውን፡ይስጠን፤
ኤሮ፡ወዲያ፡እባካችሁ፡
ጣሙ፡የት፡ላይ፡ነው፡
እንዲህ፡ከጉንሮ፡ኢጉንሮ፡
የምንሻማው፤
ለሕይወት፡ነቀርሳ፡
ለዓለማዊ፡ጠንቅ፡
አናግቶ፡ንብረትን፡ለሚያነቃንቅ፡
ሰውን፡ለሚያጣላ፡ለሚያነጣጥት፡
አፉላ፡ለሚታጨድ፡ነገራዊ፡ምርቅ፡
እልኩ፡እሰ፡ለማለቱ፡ለማተናነቅ፡
ነወይ፡የምንጥረው፡
ላብ፡ኅብ፡የሚሰን፡
ከእግር፡እስከራስጌ፡የሚያናግረን፤
ስጦታ፡ነው፡ሐሉኝ፡
ላንዲንዱ፡ቴንጠኛ፡
እቢቱ፡ለማይውል፡
ሊሊት፡ለማይተኛ፤
ስጦታ፡ነው፡ለሉኝ፡

ካንዱንዱ፡ለጩኛ።
ለሰፈር፡አውዲልዱዱ፡
ለሥራ፡ለግመኛ።
ስጦታ፡ነው፡ሌሎች፡ካንዱንዱ፡ፈጣን።
ለእግረ፡ጉንዱሽ፡ሐሳብ።
ካብዛኙ፡ለሳን፤
(ነፃ፡ሰው፡ሲነድ፡ሰው።
እየው፡ተመልከት።
ሲከንፍ፡ሲሯሯጥ።
ሳሳስችሉ፡ብሎት፤
ኧረ፡አግተረተረው።
ትንፋሽ፡አሳጣው።
አሳቀመው፡በጆሮው።
ሲንር፡የገባው፤)
አሳስኪድ፡አሳስቆም፡አሳሠራ፡ብሎ።
መርዝ፡እንዲቀመስ።
ወዴያ፡ወዲህ፡ከንፎ።
የሰማውን፡ወሬ።
እንዲያ፡መከራ፡አይቶ።
ምነው፡ለጥቂት፡ጊዜ።

አርግዞት፡ቢያድግ፡
ያጥኒት፡ልጅ፡አርጎት፡
ከሚያወናብድ፡
ኧረ፡ወዬ..ያ፡ወዬ..ያ፡
ኡዬ..ያ፡ኡዬ..ያ፡ኡዬ..ያ፡
ሰው፡ነኝ፡እንኳሰን፡
ለዚህ፡ለዚህ፡ሙያ።

ጥር፡፲፱–፲፱፻፷፫ ዓ፡ም፡

## እራሴ፡ ለራሱ፡

አጅብ፡የዋልኝበት፡ተረ፡አረም፡በሌቶት፡
አዞሮ፡እማያዩ፡ጠፍቶ፡የሚያስብበት፡
እራሴ፡ለራሱ፡ብቻ፡ሲሆን፡ካሣ፡
ሰው፡ለሰ፡ብየ፡እኔ፡እንዲያው፡ዱከምኩሳ።
እስከ፡ጊዜው፡ድረስ፡ስቀኝ፡እናስተ፡
እድሜ፡እንደሁ፡አያልቅም፡ሳያጨማልቅ፡

የካቲት — ፲፱፻፶ ፡ ዓ ፡ ም ።

## ጥቁር

ጥቁር — ጥቁርቁርቁር ።
ዙሪያዬ ፡ ሰማዩ — አገቱ ።
የምትዘራበት ፡ ማኅፀን ።
የምትኖርበት ፡ ጎጆ ፡ ጥቁርሽ ።
የምታበሰብስበት ፡ መቃብር ፤
ቀን ፡ ቀን ፤ ጥሳ ።
ሰማያዩህ ፡ ተሳሳ ፤
ማታ ፡ ማታ ፤ ጭለማ ።
ዓይን ፡ አሸፍነህ ፤ እንዳትታማ ፤
እንዲህ ፡ ከሆንክ ፡ ታዲያ ፡ በደፋ ፡
ለማን ፡ ጸልዩ ፡ በማን ፡ ልከፉ ?

ሚያዝያ — ፲፱፻፶፫ ፡ ዓ ፡ ም ።

ወጣቱ ፡ ፈሳስማ ።

ዩ መ ፡ ነፍስ ፡ ካሳቸው ።

ፏ

በውቀት፡የሳቅሃቸው።

ዠምዧማው፡ፈሳስማ፡እስኪ፡ንገረኝ፡
የዋዋ፡ጎደ፡ዋና፡ምን፡እንዴሚያስመኝ፡
እጥንተኽዋሉደ፡ሳትገባ፡በሬቱ፡
የጅና፡ እግርን፡ሥራ፡
አርገህ፡በሥራት፡

ዠምዧማው፡ፈሳስማ—
ታዬያ፡እስኪ፡ንገረኝ፡
አድርገህ፡ግጮሩ፡

ሰጠምህ፡ተንሳፈፍክ፡
እንዴት፡ነው፡ነገሩ ?
ወይንስ፡እዟረቱ፡ሳበችህ፡እግሐሩ ?
ከየትኛው፡ነሣ፡ዘለው፡ከገቡት፡
ወይስ፡ዴሞ፡እጥንተው፡
በቀጥ፡ካወቱቱ።

ዠምዧማው፡ፈሳስማ፡
እንዴት፡ነው፡ነገሩ፡
የዋና፡ምሥጢሩ ?
እስኪ፡አንቆርቁርልኝ፡
እኔም፡ብረዳው፡

ለስረኛ፡ ቢሆነኝ፡ እንድከተለው ፤
ግን፡ እንጂ፡ አይመስለኝም ፡
አሳጊጊኸኝም ፡—
የሚያጊጊ፡ አይዪለም፡ አሰናዘርህ፡
የገር፡ አመታተር፡ የጅ፡ አነሣሥህ —
ኀብቶ፡ ጥልቱ፡ ስቱል፡ የዋኘህ፡ መስሉህ፡
የነፋህ፡ ይመስሳል፡ የገባው፡ አየር፡
ዴርሶ፡ እንዴሚያውቶበት፡
ስትገናተር ።
ዞምሂማው፡ ፊሳስማ፡
ታዪያንን፡ ታዪያንን —
እስኪማ፡ ንገረኝ፡ ከየትኛው፡ ነህ፡
ተሳስተህ፡ እውነት፡ ዛሬ፡ ቢወጣህ ?
ቁሽርሽር፡ ተሻራ፡
ነሆደ፡ ብክንክን፡
እንግተ፡ ገቶል፡ ሰው፡
የጊዜው፡ ምጥን፤
ወይስ፡ ካልተጠሩ፡ ከነ፡ ከሴ፡ ጋር፡
ካንገቴ፡ ማወዛወዝ፡
ከጅ፡ ማንጨፍረር ?

ታዲያ፡ እንዲያው፡ ባባትህ፡

እስኪ፡ ሊመልከቱኝ፡

አዙሮ፡ እሚያይ፡ አንገት፡

ምናልባቱ፡ ቢገኝ ?

አይመስለኝም፡ ከቶ፡

በውነቱ፡ ያየህ፡

አዬ፡ ሰውነትህ፡ እየጋረደህ፤

ታዲያንን፤ ታዲያንን፡ ወጣት፡ ፈጎስማው፡

ኘገረኝ፡ እባክህ፡ እስኪማ፡ ልስማው፡

ሰው፡ ከቶ፡ አይችልሞይ፡

ሲርቅ፡ ካፍንጫው ?

ጥረንና፡ ግረን፡ ሰፍተንም፡ ዴክመን፡

ዘረን፡ እዚያው፡ ነሞይ፡

አበረታችን ?

ክበረቱ፡ የማያልፍ፡

ክበረት፡ አፍንጫ፡

ነወይ፡ አውቀታችን፡

የኋቱ፡ ጎይ፡ አልጫ ?

ታዲያ፡ እንግዲህ፡ እንዲያው፡

አዬ፡ ለመሆን፡

ምንድነው፡ሕይወትስ፡
መማር፡መሠልጠን ?
እዩ፡ነው፡በውነቱ፡የመጣቱ፡እድል፡
በሽ፡ተዋውሶ፡ዝም፡የሚያስከፍል፤
የድኋ፡ፍጭርጭር፡
የንሐ — ንሔው፡
ሰው፡የሚገርመው —
አሻሮረኝ፡እምቢ፡
ብሎ፡እንኳ፡ሳይቀር፡
ዋይ፡ብሎ፡መውጣቱ፡
በኃጢአት፡በር፤
አይገርምህ ምሳ፡
አንተስ፡ያገር፡ልጅ፡
በኃጢአት፡ተፈጥረህ፡
በዲ፡ስቶዋጅ፤
እኔንስ፡ገረመኝ፡
በጣም፡አዘንኩኝ፡
የኃጢአት፡ፍሬ፡እዩ፡መሰሰኝ፤
ትጸከምኩ፡ፈዘዝኩኝ፡
ኢካሌ፡ከዪኝ፡

ጨርሶ፡ከሚጉኅ፡
    አልወጣም፡እለኝ።
መልካም፡ሆኖ፡ሳየው፡
    ለሱ፡በሬናው፡
ለመንገዬ፡ከክን፡
    ሆነብኝ፡ጥጎው።
ምን፡ኅድርግ፡መቼስ፡
    ነፍሴ፡ትጣሰው።
ሥጋ፡ስጋት፡ሆኖ፡
    በረኝ፡ከዘጋው።
የኔስ፡ይሁን፡በጄ፡
አንተስ፡አቶ፡እከሌ —
ያሚረካው፡ሥልጡን፡
    አዋቂው፡ወጣት፡
እንዴት፡ይመስልሃል፡
    የዋና፡ኅብልሃት ?
አቋርጠህ፡መጣሆይ፡
    በርትተህ፡ግሖሩን፡
ወይስ፡ተዘቀዘ፡ጊስምህ፡ራዷን ?
    እባክህ፡ንገረኝ፡የት፡ጎይ፡ዴከመህ።

ግዙፍ፡ሰውነትህ።
ከየት፡ሳይ፡ከዳህ ?
ደግሞስ፡ካልደከመህ።
ዋኝተህ፡ከመጣህ።
ከፎሴው፡ሰይቹ፡እንዴት፡ልወተህ ?
ቦሰል፡ያለ፡ሱሪ፡ዘርፈፍ፡ያለ፡ኮት።
ሰቀቅ፡ያለ፡ሸሚዝ፡ወፍራም፡ክራባት።
ነወይ፡ምልክትህ፡ሰሌዳ፡ታርጋህ።
እውቀት፡ፍልስፍናን።
የሚያበስርልህ ?
ወይስ፡ከምበል፡ከምበል።
ያረማመድ፡ሞድ።
ሰፋ፡ሰፋ፡ያለ፡እርምጃ፡መውሰድ ?
ፀጉርን፡እጉ ተሞ፡ወደ፡ሳይ፡መናር።
ወይንስ፡ሰይምሰል፡ሳገር፡መቆርቆር ?
እስኪ፡እየትኛው፡ሳይ።
ነው፡እውቀት፡ያለው።
እልብስ፡እጉ፡ተናው፡ወይስ፡እርምጃው ?
አባክህ፡ያገር፡ልጅ።
ንገረኝ፡ልስማው።

ምንድነው፡ልብህን፡የሚጐትተው፧
ኦፔላ፤ዱኬዲብልዩ፡
ቸብሮሴት፡ታኖስ፡
ቮልስ፡ዋገን፡ሬክርድ፤
ፊያት፡ማርቼዲስ፤
ነወይ፡እልብህ፡ውስጥ፡የተረገዘው፤
በሐሳብ፡ተጸንሶ፡ዱግሬ፡አሚወልዱው፡
አውቀትህ፡ያለበት፡ቦታ፡ተስሞኛል፡
ጊዜ፡ምራን፡ምራን፡—
ጊዜ፡ምራን፡እንጂ፡እሰዚያ፡ጨንቆኛል።
አንተስ፡እንግሊዙ፡
ባለ፡ፋሽኮ፡ቁርጡ፡
ባላጭር፡ኮትና፡ባለ፡ፔፖ፡ቁንጡ፤
ባለ፡ወፍራም፡ካፖርት፡
ባሳጭር፡ቦሌው፡
ድክም ክምክም፡ያለች፡
ሸሚዝ፡የሸመዝከው፡
ከራባትህ፡ሳልቶ፡
አታች፡ያዘቀጠው፡
ንቅል፡ንቅል፡ባዩ፡ጊዜ፡የሌለህ፡

እስኪ ፡ እምኝህ ፡ ሳይ ፡ ነው ፡
ያለው ፡ እውተትህ ?
እልል ፡ ክራባትህ ፡ እችኩል ፡ አግርህ ፡
ነወይ ፡ የሚገኘው ፡ ሥራና ፡ እርምጃህ ?
ምሥጢርክን ፡ ንገረኝ ፡
እባክህ ፡ አጫውተኝ ።
እባክህ ፡ ንገረኝ ፡ እኔ ፡ እንዲግዝህ ፡
ስትቆም ፡ እመንገድ ፡ ሳይ ፡ እንዲቀበሉህ ፡
ውስኪና ፡ ብራንካ ፡
ነወይ ፡ ቤንዚንህ ?
እባክህ ፡ ንገረኝ ፡
እኔም ፡ ወንድምህ ፡ ነኝ ፡—
አንተስ ፡ አንተስ ፡ ዴሞ ፡
የማያልቅ ፡ ወጪህ ፡
የሚሰማህ ፡ ካለ ፡ ሥራ ፡ እሚያስረሳህ ፡
ጆርመን ፡ ጆርመን ፡ ሲሉህ ፡
የሚያናግርህ ፡
በረጅም ፡ ብርጭቆ ፡ ቢራ ፡ መሰምከክ ፡
ለምዱህ ፡ መጣህና ፡ የምትታወክ ።
ሐይቁ ፡ መዋኛው ፡ መናፈሻው ፡ ቦታ ፡

ሲያዛጋህ፡የሚውል፡ባንዴየ፡ትዝታ።
እንዴት፡ሊትገፋው፡ነው፡
ያገርህን፡መንገድ፡
ባስታወስከው፡ቍጥር፡
የኋሊት፡ስትሄድ።
ልትገፋ፡ይሻሃል፡
ልብህ፡ይከጅሃል፡
እንተስ፡ዱግሞ፡ሲሳው፡
ባለ፡ቍንን፡እሥሩ፡
ባለ፡ልምጥ፡ፀጉር፡ባለ፡ቡርሽ፡ዘሩ።
ባለ፡እንቶ—ጭንቅ፡ኮት፡
ባለ፡ልጥፍ፡ሱሪ፡
የዱንኪራ፡አጥቴው፡ውዝዋዜ፡መሪ።
በተረከዝ፡ተነሽ፡ወዲ፡ኋይ፡መጣቴው፡
መጠጥ፡ምን፡ሻ፡ቢልህ፡የማትዱሬረው፡
ፓሪስና፡ማርሴይ፡ትምርት፡የጨረሰከው፡
እምንህ፡ኅይ፡ነዋ፡አውተትህ፡ያለው፡
እውዝዋዜህ፡ኅይ፡ወይስ፡እቷንቷው ?
አሁንስ፡ጨነቀን፡
የምንሠራው፡ጠፋን።

የጋላ፡ጉራጊው፡የትግሬው፡ጠባይ፡
የወላሞውና፡ያማራው፡ጠባይ።
የኦመቴው፡ጠባይ፡
የዞላ፡የጐፋው፡የኩሎ፡ኮንታው፡
የጊሚራው፡ጠባይ፡
የባሬያ፡ኩናማ፡ያኙዋክ፡የቆመው፡
የሱማሌውና፡ያዳሉ፡ጠባይ፡
የሸናሻ፡ቦሻ፡የከፌው፡ጠባይ።
አንድ፡ባህል፡ሆነው፡ሌትዮጵያዊነት፡
መኖር፡እንዲያሻቸው፡ስለተረዱት።
የሚሆን፡መስሏቸው፡
የሚያጎባቧቸው፡
ፍንገት፡አራት፡ባህሎች፡
ታዛቢ፡ጠርተው፡
የጦርነት፡ሜዳ፡ሆኑ፡ቤታቸው።
ጨርሰው፡ተዋጡ፡
ባህሎቻቸን፡ሁሉ፡ጨርሰው፡ቅሉ፡አጡ፡
የውጪቹ፡ዱብረው፡
አንገት፡ላይ፡ሲወጡ፡
እኛም፡ተበላሸን፡ከዚህ፡የተነሣ፡

ያለ፡የሌሰውን፡ሁሉን፡እስከገረሳ፤
አጉል፡መንጠራራት፡ሆነ፡ለሥራቸን፡
አጉል፡መገደርደር —
አጉል፡እውኝ፡እውኚ፡

አንገትን፡ማሾር —

አጉል፡መዘባነን፡አንገትን፡መምዘዝ፡
እነ ታጥበህ፡እርዳኝ፡
ታዲያ፡ታጥበህ፡እርዳኝ፡
ታጥበህ፡እርዳኝ፡ሆነን፡

አንዱ፡ሳይያዝ፤

ታዲያ፡ይህ፡አይሆንም፡
የሚሠምር፡አይመስልም —
የምን፡ሰማይ፡ሰማይ፡አንጋጦ፡መሔድ፡
የምን፡ሰበር፡ሰካ፡ሰው፡ማወናበድ፡
እግር፡የሚረግጠው፡ሳይገኝ፡መንገድ፤
ምንድነው፡ትርጉሙ፡ያፍንጫ፡መንፋት፡
ጥርስን፡እያሳዩ፡ግንጁት፡መንከትከት፤
ምንድነው፡ትርጉሙ፡

ዓይን፡አፈር፡መምሰል፡

ተሽቆጥቁጠ፡ግብቶ፡ነገር፡መጉልጉል፤

ምንድነው፡ትርጉሙ።

ያየር፡ኃይ፡መናር።

አገጀትን፡ጠፍሮ፡ያጉል፡መሽተርቀር ?

ምንድነው፡ትርጉሙ፡ሳይለቁ፡መሳቁ።

ውጣ፡አትውጣ፡እያሉ።

ለሚቴ፡የማነቱ ?

እኔስ፡አልገባኝም።

የገባው፡ቢኖር።

ይህ፡ነወይ፡ሥልጣኔ።

ዘዴው፡የመኖር ?

መልከ፡እስሆይ፡ታዱያ።

ፈኅስማው፡ወጣት።

ለዚህ፡ሁሉ፡ትርኢት፡ለኑሮ፡ጉቶቶ ?

እባክህ፡ገገረኝ፡እስኪ፡ያገር፡ልጅ።

የጀርመን፡ፈረንሳይ፡ያሚሪካን፡ቱጅ።

ባፍ፡እንግሊዝ፡መሳይ፡ቡና፡በወተት።

እሁሉም፡አሰሁ፡ባይ።

ግንጣይ፡ፍጥረት ፤

ያገር፡ፍቅር፡ይዞ፡የሚያስጨንትህ።

ልብህ፡ሚ፡ራስህ፡ዒ፡ብሎ፡እሚያከነፍህ።

ነገረኝ፡ያገር፡ልጅ፡

እስኪማ፡እባክህ?

የልብህን፡ሙያ፡

አፍህ፡ሲቀድመው፡

ለሥራ፡እሚቀርህ፡

ኋላ፡ምንድነው?

ለፍልፈህ፡ለፍልፈህ፡

እንፋሎት፡ስታጣ፡

እዴረሳዘሞዴ፡

ሥራ፡እሚሉት፡ጣጣ።

ድሃን፡ድህነቱን፡ከምትነግረው፡

ያገኜቱ፡በሽታውን፡ከምታሰማው፡

ለምን፡በተማርከው፡

አትደግፈውም፡

ቅዝቶ፡ሆነ፡ህበቱ፡ከሚያጣ፡ሰሳም።

ቲግን፡መተናነቅ፡

ዴዎ፡መዛቅን፡

አሹቅን፡መከርተፍ፡

ቆሎ፡መቃምን፡

በሽታ፡ነው፡እያልክ፡

በሽታ፡ አትስጠው፡
ስትነግረው፡ ነውና፡
ሆዱን፡ የሚያመው፡
ካዘንክ፤ ከተሰማህ፡ ካንጀት፡ ከልብህ፡
የማይጠቅም፡ መስሎ፡ አንተ፡ ሲታይህ፡
ጤናና፡ ሰውነት፡ ጣሚና፡ ጣሬጥ፡
መስሎ፡ የታየህን፡
ሰጥተኸው፡ ይምረጥ።
አስዚያ፡ ካልቻልህ፡
ይህን፡ ለመስጠት፡
አፍክን፡ ይዘህ፡ ቁጭ፡ በል፡
አታብዛ፡ ተረት።
ባንክሮ፡ ተዘክሮ፡
ሳይ፡ ሳዩን፡ መፍሰስ፡
ባባቶች፡ ዴም፡ መስሎ፡
ፍሬ፡ መከሰስ፡
ምን፡ ዓይነት፡ ሙያ፡ ነው፡
ምንስ፡ ፍሬ፡ አለው፡
አትኩሮ፡ አውጠንጥኖ፡
ልብ፡ ካረገው።

የሥልጣኔ፡አክርማ፡ብቻ፡እየቀጨን፡
ስንዴጸና፡ወስፌ፡በቴ፡መሰሰን፤
እስኪ፡ስንቆቻችን፡መሶቦች፡ሠራን፡
ለእንጀራ፡ማኖሪያ፡
ለሕይዎት፡መድኅን፤
ደግሞስ፡ከስንታችን፡አገልግል፡ተገኘ፡
ለረጅም፡ጉዟችን፡ስንቅ፡ለተመኘ፤
ለሚሰማው፡ግራ፡ለተመልካች፡ዚቅ፡
እንዴህ፡እርጉም፡የለ፡
በጥበብ፡መዝለቅ፤
ታዲያ፡ለዚህ፡ለዚህ፡
ምንድን፡ያዴክማል፡
ወስፌን፡ብቻ፡አሹሮ፡
ስንዴዴን፡ታቅሮ፡ሰፌ፡ለመምሰል።
መለፍለፍ፡አይበቃም፡
የባጥ፡የቆጡን፡
መሥራት፡ያስፈልጋል፡
ለመግለፅ፡ሙያን፡
መናገር፡መናገር፡
ሰውን፡ማጭበርበር፡

መስፍስፍ፡መስፍስፍ፡

አፍን፡መተርተር፡

ባርኽ፡ኩርኽ፡ወሬ፡

መታሸት፡መናር፡

ምንም፡ጥቅም፡አይሰጥ፡

እድገቱ፡ለሀገር፡

እስከ፡መቼ፡ድረስ፡በማገር፡እያልን፡

እስከ፡መቼ፡ድረስ፡በልፕ፡ተይዘን፡

መቆምን፡ሳንማር፡እንኖራለን፤

እስኪ፡መቼ፡መቼ፡ማዘን፡እናቱም፡

እራስን፡በመግታት፡

እንድንችል፡ለቅም።

ሁል፡ጊዜ፡አጨብጫቢ፡

ሁሉ፡ተመልካቹ፡

ሁል፡ጊዜ፡ተቺ፡ሁል፡ጊዜ፡ተተቺ፡

በመሆን፡ዴስ፡ብሎን፡የምንኖረው፡

ሰዎች፡እስከመቼ፡እስከመቼ፡ነው።

የኛስ፡ተግባራችን፡መሆን፡ያለበት፡

ማስገኘት፡ነው፡ፍሬ፡

እንደዛፉ፡ዓይነት፤

ይቸረር፡በሰሬው፡የሥልጣኔ፡መልካ፡
የተጠማ፡ሁሉ፡ጠጥቶ፡እንዲረካ።
ይዋጃን፡ያጠጣን፡በየመስኮችን፡
ይቱረፍረፍ፡ይኩረፍረፍ፡
ይሙላ፡ገንዳችን፡
ጥምትምቅምት፡አርጉ፡
በርችስችስችስ፡አርጉ፡
ሥራ፡እስኪያሠራን።
ገረግንቡ፡ይሙሉ፡
የዕውተት፡ልባችን፡
ይሰራጭ፡ያጠጣን፡
ሳይነጥፍ፡ያርካን፡
ዪም፡እንሰት፡በሽታ፡
ሆሞ፡እንዲያመን።
ያገር፡ፍቅር፡እሳት፡
ያንድድ፡ያግመን፡
ይግራጥሬጥ፡ይያያዝ፡በየልባችን።
ብር፡ነጥሮ፡አገርን፡
እስኪያሳውተን፡
በመሥራት፡እናሳይ፡ወሬ፡አይግደለን፡

እግራችን፡ይፍታታ፡
ይሠራ፡ስእምሯችን፤
በመሥራት፡ነው፡እንጂ፡
ተሰም፡መለወጥ፡
በመዘር፡አይደለም፡
አብሮ፡በመኖጥ፡፡

ግንቦት — ፲፱፻፷፬ ዓ፡ም፡

## እምቧ፡በሉ፡ሰዎች፡

እንዴት፡ነው ነገሩ —
ካልሆነ፡እምቧ፡በሉ፤
ሰው፡እንዴት፡አያውቅም፡
የልባችንን
ሠልጥኑ፤ ሠልጥኑ፡ተማሩ፡ተማሩ፤
እያለ፡ሌት፡ተቀን፡የሚያጥክበን፡—
እንዴት፡አይገባውም፡እንዴሳቃትን፡

አቶሚክ፡ሳተላይት፡
ለመኖር፡ሠርተን፡፡
ለልሰማሞይ፡ምነው፡
ያረር*፡ተማሮች፡
ሮኬት፡ተኩሰው፡ዝናቸው፡ሲናኝ፤
አሳነበበሞይ፡በየጋዜጣው፡
ኮሚቴ፡እንኳ፡ሳይቀር፡
ተቋቁሞላቸው፡
በሰፌው፡ለመሥራት፡
አቅድ፡ለማውጣት፡
ታውቆ፡እንደሚያስፈልግ፡
ገንዘብ፡ወደዚያው፡
ከየማዕዘኑ፡ሲጎርፍ፡መዋጮው፤
እንዴት፡ነው፡ነገሩ፡የሚጠራጠረው፡
የኛን፡ሥልጣኔ፡
ፍጥረት፡የማያምነው፤
እንዴት፡ነው፡ነገሩ፡
ተምረን፡ተምረን፡አውቀት፡አግኝተን፡
ሠልጥነን፡ሠልጥነን፡
አቶሚክ፡ሠርተን፡



* በመጀመሪያው ግጥም ውስጥ "የኮሌጅ ተማሮች" ይል የነበረው ተለውጦ ነው።

እንዲናጋሳኪ፤ እንዲሂሮሽማ፡
አገር፡ካልመተርን፤
ሳያስጐብለን፡ነወይ፡እኛን፡ሠለጠን፡—
እንግዲያስ፡እንዲዚህ፡
እስከዚህ፡ከሆነ፡የሰው፡ዓሳማው፡
እምቢ፡አንሰለጥንም፡
ፍጥረት፡ይወተው፡—
ቆርጠናል፡በጭራሽ፡እንዳናስገባው፡
ይህን፡ሥልጣኔን፡
እኛጋ፡ሲመጣ፤
መልኩ፡ተለዋውጦ፡ስላሳገኘነው፡
ሰው፡እንዲሚለው፡
ወኔን፡አቀዝቅዞ፤
ፍርሃትን፡አንግሦ፤
አፍን፡የሚያንጣጣ፡የልስልስ፡በትር፡
እንሻም፡ጨርሶ፤
ጨርሶ፡እንዲገባ፡ከወንዶች፡አገር፡፡—
እራሱም፡ይወተው፡
ሥልጣኔም፡ይወተው፡
መንገዱ፡ሳይመታው፤

የጤፍ፡ቅንጣት፡ያህል፡
እንዲማንቆጥረው።—
ዲግሞስ፡መጀመሪያ፡
እንዴት፡ቢንቀን፧
እንዴት፧እንዴት፧እንዴት፧
እንዴት፡ይደፍረናል፡
ዓይናችን፡እያየ፡ሞተናል፡ቆመናል።—
ጋባ፡ቢሳዋ፡ልጅ፡ድርሽ፡እስኪ፡ይምጣ፡
ባናንቆራጥጠው፡ባናጎየው፡ጣጣ።—
ይህ፡ኬሳ— ሰባሪ፧
በሰው፡አንጐል፡ጠልቆ፡
እንዲያው፡ሰምናልባት፧
ቀራጮች፡ሳያዩት፡
አምልጦ፡እንዲሆን፧
የቁንጫ፡ኩርኩም፡
እሚያደማበት፡
ወዘኔ፡ቤት፡መጣል፡ነው፡
እጅ፡እግሩን፡አሠረን፧
ዋጋ፡እየቀነሰ፡እንዲያከስረን።—
እናጥፋው፡በጭራሽ፡

ከሥር፡መሠረቱ፤
ማን፡ተተጥቶ፡ያውቃል፡
እውቀት፡በማጥፋቱ፤
እናጥቃው፡ጠንክረን፡
ከሥር፡ጀምረን፤
ቀሊዩ፡ጥዛና፡ተረት፡እያዘወተርን፤
ሞያም፡ባር፡ባር፡ብሎን፡
እንርሳ፡ሁሉን፤
ድኅነት፡ከሰው፡ለንበልጥ፡
ዘሎ፡እንዲያገኘን፡—
እውቀትና፡ማግኘት፡
ለድገት፡መጣጣር፡
ይቆጠር፡ከኃጢአት፡
ከቢሳሽ፡ነገር፤
ጥሩ፡ሰው፡ይወሰን፡
በማይጥር፡በማይግር፡
ወጥነቱ፡ታውቆ፡
ሰው፡እንዲያሰጨንቅ፡
ሠራውን፡በልቡ፤ሞያውን፡በልቡ፤
ጨቁኖ፡በሚኖር —

በዚህ፡ዓይነት፡መንገድ፡እንታገሰው፡
ጎርማ፡ሞገሳችን፡
ቀድሞ፡ካልጣሰው።—
እተማመናለሁ፡ሥልጣኔ፡ሲጠፋ።
ሰውም፡አብሮ፡መጥፋቱ፡
ጎዲጁ፡ቢገጥመው።
ቀዲም፡ብለን፡እኛ።
እንስሳ፡በመሆን፡እንዲምንግታው።—
እንሁን፡እንስሳ፡ይመ—ነፍስ፡ያለን።
ሌላው፡ቢቀር፡እንኳ።
ሞተን፡ከመነሳት።
ከሌላ፡ዓለም፡ስታይ።
ድንገት፡ብንድን።—
ደግሞስ፡መጀመሪያ።
እንስሳን፡ከኛ፡ጋር፡በማወዳደር፡
ማነው፡መብቱ፡የሰጠን፡እራስ፡የማኖር።
እንዴያው፡ስመሆኑ።
ምናልባት። ማን፡ያውቃል።
አውቀው፡እንዴሆን።
እንስሳት፡ዝም፡ብለው፡የሚታረዱን።

ምናልባት፡ማን፡ያውቃል፡
መስዋዕትነት፡
ፈልገው፡እንዲሆን፡የሚሰታዩት።
ምናልባት፡ማን፡ያውቃል፡
የሰማይ፡መንግሥት፡
እሸቴው፡እንዲሆን፡ሞኝ፡የመሰሉት፡—
በናንተ፡አስተያየት።
አውቆ፡መሰቃየት፡ሞኝ፡ካሰኘማ፡
ለሰው፡ምግብ፡መሆን፡
ካረገ፡እንሰሳማ።
ክርስቶስ፡እራሱን፡ሰማዒን፡ሲችል።
ምነው፡ምነው፡ምነው፡
አሳልፎ፡እራሱን፡ሰጠ፡ሲሰቀል፡፡—
የሱን፡መታሰቢያ—ሥጋወ፡ደሙን።
ቀምሰን፡እንድናለን።
ነው፡እምነታችን።
ነገር፡ግን፡እንስሳ፡በደም፡በሥጋቸው፡
በቆዳ፡በሞራ፡መሳ፡አከሳታቸው፡
ሲያቆዩን፡ፈውሰው፡እየመገቡን።
እንዴት፡ለማለት፡ቻልን፡

እንበልጣለን ።—

ጨርሶ ፡ አይመስለኝም ፡

ይህ ፡ አስተያየት ፡

ካፍንጫው ፡ የራቀ ፡ የምንኮራበት ።

ስለዚህ ፡ ምናለ ፡ ለስህተት ፡ ስህተት ፡

በእንስሶቹ ፡ መንገድ ።

እንለሳ ፡ በመሆን ፡ ኑሮን ፡ ብንገምት ።—

እምቧ ፡ በሉ ፡ ሰዎች ፡ እንመለሰው ።

እንዴ ፡ ጋብሉ ፡ ሐንዶች ፡

ሥልጣኔ ፡ እንዴጠሉት ፡

ሁሉን ፡ እንጥሳው ፡

ጋብሉዎች ፡ እንዴሉ ፡

ልጆች ፡ አይቀጡ ፡ ይግጡ ፡ ይቀበጡ ።

እንዴውሬ ፡ እንዴሰው ።

እንዲሻቸው ፡ ይውጡ ።

ማንም ፡ መብት ፡ የለውም ፡

እነሱን ፡ ሊቀጣ ።

ድንገትም ፡ ቢያስፈልግ ፡

ነው ፡ የቂስች ፡ ጣጣ ።

ነገር ፡ ግን ፡ ቂሶቹ ፡

ቀጥተው ፡ መተጣተን ።

እንደያውቁ ፡ ጠንቅቀው ፡

ሁሉ ፡ እኩልነቱን ።

ልጅም ፡ በበኩሉ ፡

ቁሱን ፡ ይሸምትር ።

የቄስ ፡ ልቡ ፡ ሞልቶ ፡

አድገት ፡ እንዲያምረው ፡

ለሙ ፡ እንዲደታወቅ ፡

እንዲያስቸግር ፡፡

እንደዚህ ፡ ይሳሉ ።

ታሪከኛ ፡ ነገድ ፡ ሠልጡን ፡ ያበሸቁ ፡

ባሞቲ ፡ መምረጫ ፡ መሳቸው ፡ የሳቁ ።

በጣም ፡ ይደንቃሉ ፡—

ልጆችን ፡ በመቶጣቱ ፡ እንኳ ፡ በተንሹ ፡

ቄሶች ፡ ከሰው ፡ መብለጥ ፡

መስኂቸው ፡ የሚሹ ።

ልጅም ፡ በበኩሉ ፡ ተቀጥቶ ፡ እንዲቀጣ ፡

በማድረግ ፡ አጠፋ ፡ የመብለጥን ፡ ጣጣ ።

እንግዲህ ፡ በቁርጡ ፡

በቁርጡ ፡ ያዲም ፡ ልጅ ፡

ተመልካችነት ፤

መታሰር፡መገረፍ፡ጭራሽም፡መሞት፡
ከሰው፡ሰው፡ሲልቅ፡ነው፡

የሚደርስበት ፤

ታዲያ፡ምን፡አሰበቱ፡
በዚህ፡አስተያየት፡
ምን፡ውርደት፡አሰበት፡

ብንገፋው፡ጊዜን፡

ሥልጣኔን፡አጥፍተን ፡—
እንከሳን፡በመምሰል፡እንስሳ፡ሆነን ፡፡—
ሰዎች፡እምቧ፡በሉ፡እንመስለሰው፡
በኔው፡ጊኔ፡ደቡብ፡
በምሥራቅ፡እንደሉ፡
እንደ፡ደቡ ፡ ጉሣ፡ሁሉን፡እንርሳው ፡፡
ደጎነት፡ጨርሶ፡ካገር፡ይደምሰስ፡
ከጥፋት፡ተቆጥሮ፡

ደግ፡ዋደ፡ይከሰስ ፤

ደቡዎች፡እንደሉ፡—
ልጆች፡ይሠልጥኑ፡ሌብነት፡ይማሩ፡
ሁሉን፡ይቀሳፍቱ፡

ሰውን፡ያጭበርብሩ፣
አታለው፡ይሩጡ፡ሠፈር፡ያሸብሩ፣
መተው፡ያመታቱ፡ሰውን፡ያበጣብጡ፡
ሕብነት፡ነውና፡ለዱግት፡ለኑሯቸው፡
ሩህሩህ፡መሆንን፡
ለጋስ፡ደግነትን፡
ፍጹም፡ከልባቸው፡የሚያጠፉላቸው፡
እንደሁ፡አሰኛቸው፡
ሥልጡን፡ቢያሰጠላቸው፡—
ታሪከኛ፡ነገድ፡
በእንስሳዊው፡መንገድ፡
በጣም፡የዘለቁ፡
በፍርድ፡አለናዘር፡መላቸው፡የላቁ፡
ኑሮን፡አይተው፡አይተው፡
ካጠኑት፡በኋላ፡
ደግነት፡ነው፡አሉ፡ለሰው፡የሞት፡ጥላ፡፡—
እውነትም፡ይመስላል፣ሳውጠነጠነው፡
ልግሳ፡ደግነት፡ባይኖር፡ከቀድሞው፡
ከፉት፡ጦረኛውን፡
ምንድን፡በዋጠው፧

ሐጌ

ለክፉ፡ደግ፡ባይኖር።
ለንዝህላሉ፡ብልጥ፡
ለደንቆሮው፡ብልህ፡
ሳኟፊው፡ሰለጥ፡
ለሰነፉ፡ጉበዝ፡ሳኞኬው፡ታኞኬ፡
ለጉጂው፡ተጉጂ።
ሳዷማጭ፡ሰባኪ፡
መቸ፡ይታወቅ፡ነበር፡
ዓለም፡እንዴህ፡መልኳ፡
የሁለት፡ፊት፡ቶንኟ፡ድንገት፡መማረኳ።
ሁለት፡ፊት፡ሰሳሳት፡የሚያወሳውል፡
ሁለት፡ፊት፡ሰል—
አሳቱ—የሚያጠራጥር፡
ሁለት፡ፊት፡ሰሳሳት
የሚያሰገሳ፡ወኔ፡
እንዴ፡የተፈጥሮ፡
እንዴ፡የሠልጣኔ።
ጓራ፡ስገባባቸው፡ሰውን፡ያህል፡ሰው፡
አንዴ፡መሠመር፡ይዞ፡እንዲደጋዘው።
ስለዚህ፡ጴቦዎች፡ባቋራጭ፡ሔደው፡

ሥልጡኑን፡ሲጠፉ፡ፍጡሩን፡ይዘው፤
በነሱ፡አስተያየት፡ሥልጡን፡ዲግኒት፤
በነሱ፡አስተያየት፡ፍጡሩ፡ክፋት፡
የኛን፡ግን፡አናውቅም፡
እናንተው፡ፍቱት፡፡—
ሰዎች፡እምቧ፡በሉ፡እንመለሰው፤
ካፍሪካ፡ነገድ፡ውስጥ፡
እንዲማር ኪዎሳስ፡
እንዲ፡ በሳዒ—ሰብእ፡ሁሉን፡እንርሳው፡፡—
ሰው፡በሉች፡እንዲሉ፡—
እንዲተወለዱ፡ካሉም፡እንዲመጣ፡
ስለሚጠብቀው፡መከራዩ፡ጣጣ፡
አሸዋ፡እንዲያጎምጥ፡
ማስለመድ፡ነው፡ልጅ፡
እንዲያውቀው፡ተግባሩን፡
የኑሮን፡ግዴጅ፡፡—
አሸዋን፡ማጎመጥ፡
ጎንቃው፡ካልዴሬረ፡
ቀስ፡በቀስ፡በጥርሱ፡
አጥንት፡ካልሰበረ፤

አይቀርብም፡ጩርሶ፡
ስታኅቅ፡ምልመኅ።
ሰውን፡ያህል፡ነገር፡
አባሮ፡እንዲበኅ።
ማን፡ያውቃል፡ምናልባት፡
ምን፡እንዲታያቸው፡
ኑሯቸው፡እንዲሆን፡
እንዲህ፡ያሰኛቸው።
ማን፡ያውቃል፡ምናልባት፡
ውቅያኖስ፡መጦ፡
ጨጨ፡ድንጋይ፡ሆኖ፡ትባቱን፡ሰውጦ።
ጨው፡ያሰበት፡ነገር፡
ሰው፡ብቻ፡እንዲቀር፡
አይተውት፡እንዲሆን፡
ባኅብ፡መነጥር።
ማን፡ያውቃል?
ታሪከኛ፡ነገድ፡በእውቀት፡የዘለቁ፡
በልጅ፡አስተዳደግ፡መኅቸው፡የኅቁ።
ያለምን፡ጥንካሬ፡ያለምንም፡ካኔ፡
ልጅን፡ሲያስተምሩ፡

ለሸዋን፡ቀስ፡በቀስ፡
በማታም፡ጀመሩ፤
ካለም፡ጋር፡ያለውን፡ታላቅ፡ጦርነት፡
ካለም፡ጋር፡ያለውን፡ጠብና፡ግጭት፤
እንዲያውቀው፡አረጉ፡
ለሸዋ፡ለቀመው፡
ሰውቹ፡እንዲገባበት፡
ገብቶ፡እንዲደቆጨው፤
ጥርስ፡የሌለበት፡ድድ፡የሕፃናት፡ሳንቃ፡
ለጋው፡ያልጠበቀ፡የተፈጥሮ፡ውርቃ፤
ካሸዋ፡ሲታገል፡ግባ፡አትግባ፡ብሎ፤
ያለበትን፡ፍዱ፡ለይቶና፡አስተውሎ፡
እንድናውቀው፡ያሻል፡
የዚህ፡ዓለም፡ኑሮ፡እንደማይቆጨው፤
ታዩገ፡ሳይገዩ፡ሰው፡ወጥሮ፡ለሸዋው፡፡—
በኛ፡ዘንድ፡እንዲሰው፡
ግን፡እኔ፡እንደማየው፡
የሚያዘልቅ፡አይደለም፤
ፍልስፍናችን፡
የዛሬን፡ቀባብቶ፡መጭውን፡ሸፍኖ፡

መይሰል፡ልጅን።

ሰዎች፡እምቧ፡በሉ፡እንመሰሰው፡
እንዲ፡ጦቢያ፡አውሬዎች፡
ሥልጣኔ፡እንዲጠሉት፡
ሁሉን፡እንጥሳው፣
አውሬዎች፡እንዲሉ፣
የዝሆን፡ያንበሳ፡የቆርኪ፡ያነር፡
የነብር፡የግርኑክ፡የጐሽ፡የብሆር፣
የድኩላ፣ አጋዘን፣ የዋድ ምቢ፡ ዘር፡
የሒዪ፣የሳሳ፣የአንሹ፡የድሒር፣
የጥርኝ፡የሬቆ፡ሕብረት፡አቱመን፡
ሒድን፡ዪዳኖ፡ሁኑ፡ሁኑበት፡ሥልጡን።
የሚሉ፡ይመስሳል —
ወንድነት፣ጀግንነት፣
ኩራት፡ትልቅነት፡
ከናንት፡ሳይቀሩ፡
እኛን፡አርገው፡መከት፡
ጥለዋችሁ፡ሂዱ፡አውሬ፡አጅበው፡
በቀል፡ምሳስ፡ብቻ፡
የኋሊት፡ትተው።—

ሚኬ

የሚሉ፡ይመስላል፡
ባይሉም፡ብለዋል፡
እንኪያስ፡ታዲያ፡ሰውን፡
ምን፡ያንጉሳቸዋል፡
ታሪከኛ፡አውሬዎች፡

ታሪከኛ፡አውሬዎች፡
እነሱው፡ተሻሉ፡ሄዱ፡ተሰደው፡
ኮራችን፡ብልሹ፡እንዲሆን፡ዐውተው።
መነከር፣መንጨቀጨቅ፡
ቀቤ፡መቀባት፡
የወርቀና፡የብር፡ጀቱ፡አርጎ፡መኩራት፡
እንዲስቂኝ፡ነገር፡ሆነብን፡ተረተ፣
ምልክቱ፡ቀርቶ፡ጠፍቶ፡ወንድነት።
ትርጉም፡የነበረው፡ዛሬ፡ትርጉም፡አጣ፡
ሴትና፡አልኮል፡ብቻ፡ማዩን፡ስለመጣ።
ቤቷ፡ተፈልጦባት፡እንዲወጣች፡ሴሴ፡
ባሕር፡እንዲተፋው፡ዓሣ፡ዓሣ፡ነባሪ፡
ግራ፡ገባን፡ድንገት፡
ሥልጣኔ፡ጎብዘን፡
እሰው፡ማጥ፡አግብቶ፡እንዲያዱከረን፡፡—

በጣም፡የሚያሳስብ፡
ነው፡ግራ፡እሚያጋባ፡
ለሚመጣው፡ትውልድ፡
ለሚያቷቱም፡ለምባ፡፡—
እኔስ፡ግዴለኝም፡
እንስሳ፡ለመሆን፡
አንደኛ፡ደረጃ፡ለጠናቶቱያለሁ፡
ጨለም፡ባለ፡ቁጥር —
እጁን፡እግሬ፡እድርጌ፡
መሄድ፡ጀምሬያለሁ፡፡
ከእንግዲህ፡ወዲዚያ፡
ምን፡ይመጣብኛል፡
ከሌት፡ወንድሞቼ፡
ከመሰሎቼ፡እንደሁ፡ጊዜ፡ደግልቶኛል፡
የሌሊት፡ኦርበኛ፡፡
ጭለማን፡ሰዎን፡ጠላቶቼ፡ብዙ፡
ጦር፡ጬ ቤ፡መዘዙ፡
እሳት፡የሚተፋው፡ነጭ፡ለባሹ፡ሴት፡
በጠርሙስ፡ሮኬት፡እናጊ፡መሬት፡
ቀኑን፡አጨልሞ፡ሌሊቱን፡አብርቶ፡

ለማዛጊያ፡ብቻ፡ትገኝ፡ሰዓታቶቼ፡
በትዝብት፡እነማኝ፡
ቀስ፡እያለ፡ለስልቶ፤
ምን፡ላጣሁ፡ብዬ፡ነው፡
እንከቱ፡ሽርከቱ፡መጓመንመን፡መጤሱ፡
ኑሮ፡እንዲህ፡ከሆነ፡አንካሴ፡ውሳሴ፤
የሌሊት፡አርበኛ፡ለሥራ፡ግትር ትር፡
የወንድሞቼ፡ዓይነት፡
ቁርጡ፡ወታደር፤
ካወቅሁበት፡እኔ፡
እንደዚህ፡መሆኔ፤
በዚህ፡ባሁኑ፡ዕድሜ፡
በጣም፡ያኮራኛል፡
በእንስሶቹ፡መንገድ፡
ስንጓዝ፡እያየሁ፡
ሁሉ፡ያልፍልኛል፡፡
ሆድ፡ሲያውቅ፡ዶሮ፡ማታ —
የሰው፡ሳብ፡የሰው፡ዱም፡
ገንዘብ፡አንተርሶ፡
ሆድ፡ሲያውቅ፡ዶሮ፡ማታ፡

በሴቶኖ፡ባልኮሌ፡
በእንዴሳየ፡ማየት፡
ሁሉን፡አሰባብሶ፡
የዱዱን፡ውርጅብኝ፡
ሲመጣ፡አያዩት፡
ከሞትን፡በኋላ፡አናይ፡በማለት፤
እየደጎሰሉ፤ እየሸፋፈኑ፤
ከመግፋቱ፡ጊዜን፤
አይጠቅምሞ ይማ፡
በይበልጥ፡በይበልጥ —
አልኮሉን፡መርዘው፡
በጣም፡አጠንክረው —
ኑሮን፡እንቅልፍ፡አርገው፤
ቢተጬት፡ልጅን፡፡
ምነው፡ባይሆን፡እንኳ፤
ቦታ፡ይያዝ፡እንጂ —
ቀዱም፡ብሉ፡ሔይ፤
እመንግሥት፡ሰማይ —
ወይም፡ገነም፡ወርዴ፤
የተወለደ፡ለት፡ለጋ፡ቅቤ፡አጡጦ፡

ጫፌ

ጡትን፡በማሳየት፡በወተት፡አጣፍጦ፤
የድካምን፡ቦታ፤የስቃይን፡ቦታ፤
እንዲረፉት፡ቦታ፡የደስታ፡ቦታ፤
ግነቱ፡እመሬት፡ነች፡ብሎ፡አያስ፡ተረቱ፡
የማይሠምር፡የማይዘልቁ፡
የኑሮ፡ቅዠት፤
ልጅን፡ከማጌጌት፡አድጎ፡ሲረዳው፡
ደስታው፡ትካዜ፡ሆኖ፡ሲያገኘው፤
እንዲሰው፡በሎቹ፡
እንዲተወሰዱ፡
ምናልባት፡ካልኮሱም፡
ሳይሻል፡አይቀርም፤
ሳይሻል፡አይቀርም፡አሸዋ፡ማታም፡
እንዲረዳው፡ማድረግ፡
ማጣቱን፡ሰሳም።
ምነው፡ምናሰበች፡
ሰውሮች፡ብንሆን፡
እንድንኖር፡ብቻ፡
ለመኖር፡ከሆነ፡የኛ፡ኑሯችን።
በመኖር፡ለመኖር፡ባንጋጠ፡ብልሃት፡

ወራሾች፡እንድንሆን፡ወደሬት፡ገነት፡
ከሆነ፡ሐሳባችን፡
ቅድሚያ፡ጥድራታችን፡
ምነው፡ምናስበት፡
ሁሉን፡ነገር፡ብንተው —
ቢገታ፡ልባችን፡
ቢገታ፡ልባችን፡ከምድራዊ፡ኑሮ፡
ከሚያሰራችል፡ሕይወት።
ከሚሰጥ፡እሮሮ።
ጥ፡እኔን፡የሞኝ፡ብልጦች፡
መቼስ፡ምን፡ታደርጉ።
ምድራዊውን፡ኑሮ፡
ሲጠላው፡ልባችሁ፡
አሙን፡ክርስቲያኑ፡
በዝቷል፡እውስጣችሁ።
ስለዚህ፡ምን፡ቁርጥ —
ፅንድን፡በወጣችሁ፡
ለዚህ፡ዓለም፡ኑሮ፡ተጨነቃላችሁ።
እናንተ፡እንደሆነ፡
ሁሉንም፡አያታችሁ፡

ግ፲

ጥበቡ ፡ ዘልቋችሁ ።
ሌላው ፡ ቢቀር ፡ እንኳን ።
የእግዚአብሔር ፡ ትንፋሹ ፡
ከእናንተ ፡ ማለቱን —
ያውቃል ፡ ነሲናችሁ ፡፡
የሕይወትን ፡ ትንፋሽ —
የመጀመሪያውን ።
እግዚአብሔር ፡ ባዱም ፡ አፍ —
የተነፈሰውን ።
አዱም ፡ ማቱሳላ ፡
ስምንት ፡ ዘጠኝ ፡ መቶ ፡
ዓመት ፡ ኖረውበት ።
ከዚያም ፡ ሰው ፡ በርክቶ ፡
ቀስ ፡ በቀስ ፡ ጨርሶት ፡
ለናንተ ፡ የቀራችሁ ፡
ቀረ ፡ ትንፋሻችሁ ። አይበቃም ፡ ለሥራ ፡
ጎምባ ፡ ገነን ፡ ሙያ ።
ዶግጡን ፡ የቆጡን ፡
ስመለፍለፍ ፡ ብቻ —
እንዴ ሆን ፡ ነው ፡ እንጂ . .

ለማብነን፡ ተሰብቀስ—
ባፍ፡ እየተወራ፤

ምን፡ ቀረን፡ ብሳችሁ፡
ለየተኛው፡ ዓለም፡ ነው፡ የምትጥትቱት፡
ለእንቀልፍ፡ ለማይበቃ፡
ዘመን፡ የምትዩክሙት፤
ተኙ፡ እንጂ፡ በቁጡ
ሰው፡ እስኪያውቀሳችሁ፡
የሥልጣኔ፡ ጅሮች፡ በጉድን፡ እያዩ—
ደዛቸዋል፡ እንቅልፍ፡
ብሰው፡ እስኪያልፉችሁ።
ምንድን፡ በወጣችሁ፡
ምንድን፡ በነካችሁ፡
ለጥርኙ፡ ብርጉዙ፡ ተራ፡ ትንፋሻችሁ፡
አርባ፡ ዓመት፡ ለመኖር፡
ትዲ ከማሳችሁ።
ዓለም፡ ለጠፉ፡ እንዴሁ—
እንደተነበየው፡ ፍካሬ— የሱስ—
በስምንተኛው፡ ሺህ፡ ነው፡ ና፡ ድንገት፡
ያርባ፡ ዓመት፡ ትንፋሽ፡ ነው።

ብቻ፡የቀራት ።

ታዲያ፡ምነው፣ ምነው፣

ምንድን፡በወጣችሁ፡

መጓጓት፡መጋመሱን፡

በርግጥ፡ያወቃችሁ፡

ለየትኛው፡ዓለም፡

ለየትኛው፡ነገር፡

ለምኑ፡ብሳችሁ፣ አገር፡እጁችሁን፣

ታኅው ሳሳችሁ ።

የውጭ፡አሳዋቲ፡

እኮ፡እንዲያው፡ሳስበው፡

ሳወጣው፡ሳጠርደው፡

ከመሬት፡ተነሥቶ፡ነው፡የሚወቅሳችሁ፡

ጨርሶ፡ሳይገባው፡

ምን፡እንደሁ፡መሌሳችሁ ።

ምን፡ታደርጉ፡መቼስ፡

ይኸን፡ዓይነቱን፡ዚቅ፡

ይኸን፡ዓይነት፡እውነት፣

ሌታው ጠነጥኑት —

ልብ፡አእምሯችሁስ፡

እንዲያምን፡ይቻለው፡

እንዲያምንስ፡ቢሆን፡
መሞትን፡ሊያስበው፡
ተስፋ፡አያስቆርጠው?
የለም፤የለም፤የለም፡
እናንት፡ገብታችኋል፡
ያልገባቸው፡እኒያ —
እኒያ፡ባላገሮች፣ሞተዋል፡ቆመዋል፡፡
ሞተዋል፡ቆመዋል —
በዚህ፡ሁኔታችሁ፤
በዚህ፡በሥራችሁ፡
ቀርቶ፡ሳይገባቸው፡
ሥልጣኔ፡ገብቷል፡እየመሰላቸው፡
በጣሳ፤በጠጁ፤በካቲካላው፡ቤት፡
የሚቦጭቋችሁ፡፡
ምን፡ይበጃል፡ታዲያ፡
ሁላችን፡ተጣባብተን፡
አብረን፡እንድንሠራ፡

እንዲልማዱችን —

እንዴት ምህርታችን፡ እንድንንሠራራ፡

ምን፡ ይመስላችኋል፡

ምናልባት፡ ብንሞክር፡

የኋሊት፡ እየሄድን፡

ወዲሬት፡ ለመምጣት፡

የሸ ሹ፡ በመምሰል፡ አባሮ፡ ለመግባት፡

ምን፡ ይመስላችኋል፡

ብንሆን፡ እንደጥንቱ፡

በገሃዱ፤ በጓልጌ፡

ሽሽት፡ ቢያምርብን፤

መሠልጠንን፡ ሬና፡

ብሎ፡ ሰው፡ ቢያማን።

ምንድነው፡ ነገሩ፤

ሌሳው፡ ቢተር፡ እንኳ፧

ለናንተ፡ ይብላኝ፡

እኛስ፡ ዴጉን፡ ዘመን፤

ወሳሳውን፡ ዘመን፤

ኖርነው፡ የሚሉት፡

እንደሚያወሩት፤

ያልቶቱ፣ ያደዋ፡ዓሣ፡

የትኅቶል፡ምንጭ፡

ከብት፡የረጋገጠው

የከብት፡እርጋጭ፡

ባረኘጌዩ፡ቀለም፡ያኮራረሰው፣

ጤና፡ደሆነናል፡

በሙሉ፡ልባችን፡ሳናመነታታ፡

ከተቀበልነው፡

አጠራጣሪ፡መርዝ፡

ባንድ፡ሬት፡መድኃኒት፡

ባንድ፡ሬት፡በሽታ፡

ሥልጣኔ፡ብቻ፡ነው፡

ሰውን፡አጉዝሉ፡ጦቢያውን፡የረታ፤

ስለዚህ፡በፍጹም፡

ፍጹም፡አይገባኝም፡

ራስን፡ማሞኘት፡አጉል፡መብከንከን፡

ጦሱ፡ሥልጣኔ፡ካወቅን፡መሆኑን፡፡

እንግዲህ፡ምናሰ፡

ያለፈው፡አለፈ፡

ያለፈው፡አለፈ፣ አሁን፡መድኃኒቱ፡

ሥልጣኔን፡ማጥፋት፡ነው፡
ጨርሶ፡ማጥፋት፡ነው —
ከሥር፡መሠረቱ።
ምንድነው፡ነገሩ፡
ለየትኛው፡እድገት፡
ለየትኛው፡ድሎት፡ለምኑ፡ብሎ፡ነው፡
ፍጥረት፡መቸገሩ።
ለመኖር፡ መሰንበት፡
ምን፡ያሻሟል፡ ሲቃ፡
ሕይወት፡ከተገኘ፡
አንድ፡ቀን፡ሲበታ።
ታዬያንን፡ታዬያንን፡
ምን፡ይመስላችኋል፡
ቢታዩስ፡በኛ፡ዕድሜ፡የዩሮው፡ሰላም፡
የኋሊት፡የኋሊት—የኋሊት፡በመሄድ፡
እስኪያውቀው፡ዓለም፡
ምን፡ውርደት፡አለበት፡
የኋሊት፡ሔደን፡
ሊውሬ፡ብንሆን፡የሚቻል፡ሲሆን፡፡ —
ከግር፡እስከራስጌ፡

በድሎት፡ሳሸተን፤
መሥራትም፡ማሠራት፡
ሁሉም፡ታቃተን፤
ምነው፡ምናስበት፡
የፍግፍግ፡ሔዱን፡
ያሮጌ፡ዓለም፡ሕዝቦች፡
ብሉ፡ሰው፡ቢያውቀን፤
ሰው፡ሁሉ፡ሠልጥኖ፡ሥልጣኔ፡ሲረክስ፡
ሲሳ፡ዓለም፡ፈልጉ፡ባየር፡ሳይ፡ሲፈስ፡
ዱስታ፡ሕይዱለሞይ፡ሰታሪክ፡መቅረት፡
እንደኛ፡ዱንቆሮ፡ሆኖ፡መገኘት።—
ጅሬት፡የቱዱመ፡
የሬት፡እንዱኛ፡ነው፡
አኋላ፡የቀረ፡የኋላ፡እንደኛ፡ነው፡
አቅጣጫና፡ጊዜ፡ፈልጉ፡እንዱረገው፤
ምናልባት፡አንድ፡ቀን፡
ቀኝ፡ኋላ፡ሲዞሩ፡
እነዚህ፡ሥልጡኖች፡
በእውቀት፡የተመሩ፡
ማን፡ያውታል፡በድንገት፡

አንዴኛ፡ ሆነን፡

ያገኙን፡ እንዲሆን፡

እውቀት፡ ሳይደፍረን።

ጫጊካው፡ ተመልሶ፡ ሥልጣኔ፡ ጠፍቶ፡

ያውሬ፡ ዘር፡ በሙሉ፡ ወዳገሩ፡ ገብቶ፡

ሰዉ፡ አውሬ፡ ሆኖ፡

ጨርቁን፡ ወዲያ፡ ጥሎ፡

ቆዳው፡ ፀጉር፡ አብቅሎ፡

እንዲንበሳ፡ ጊፍሎ፡

የሆድ፡ መሙያው፡ ዘዴ፡

ዳይን፡ ብቻ፡ ሆኖ፡

እከ፡ በርከ፡ ተጥቶቶ፡ የሚገኅበት፡

ዘመን፡ ይመጣ፡ እንደሁ፡

ማን፡ ያውቃል፡ ድንገት፧

እናንተ፡ ያለም፡ ጨዎች፡

ናችሁ፡ እንዳለው፡

ክርስቶስ፡ ከጥንቱ፡ እንዳስተማረው፡

ያውሬ፡ ጨዎች፡ ሰዎች፡ የማንተርበት፡

ምን፡ ነገር፡ ይኖራል፡

ምንስ፡ ምክያት።—

ያሉቱቱ፤ ያደጥ፡ዓሣ፡
የትኅቶል፡ምንጭ፡
ከብት፡የረጋገጠው
የከብት፡እርጋጭ፡
ባረኘጊዩ፡ቀለም፡ያኮራረሰው፤
ጤና፡ይሆነናል፡
በሙሉ፡ልባችን፡ሳናመነታታ፡
ከተቀበልነው፡
አጠራጣሪ፡መርዝ፡
ባንድ፡ሬት፡መድኃኒት፡
ባንድ፡ሬት፡በሽታ፡
ሥልጣኔ፡ብቻ፡ነው፡
ሰውን፡አጉዝሎ፡ጦቢያውን፡የረታ፤
ስለዚህ፡በፍጹም፡
ፍጹም፡አይገባኝም፡
ራስን፡ማሞኘት፡አጉል፡መብከንከን፡
ጦሱ፡ሥልጣኔ፡ካወቅን፡መሆኑን።
እንግዲህ፡ምናለ፡
ያለፈው፡አለፈ፡
ያለፈው፡አለፈ፤ አሁን፡መድኃኒቱ፡

ጨው፡የማያስፈልግ፡

ጨው፡ነው፡የሰው፡ሥጋ፡

ዱፉር፡ብቻ፡እሚሻ፡የማይጠይቅ፡ዋጋ፤

ስለዚህ፡ታዲያገኘ፡ጊዜ፡ሲሰጣቸው፤

ምን፡ሲኖር፡ይችኋል፡የሚያስጠይቃቸው፡

አውሬው፡ሰው፡ሆኖ፡

ሰው፡እንስሳ፡ሆኖ፡

ጨውነቱን፡ፍጹም፡

በጭራሽ፡እረስቶ፡

ያውሬ፡ሰው፡ብቻ፡

ሌውቶ፡ተረዱቶት፡

ሰውን፡ያድን፡እንደሁ

ማን፡ያውቃል፡ድንገት፡፡—

ማን፡ያውቃል፡?

ዲግሞስ፡ቢሆን፡ቢሆን፡

ይህ፡ነገር፡ቢፈጸም፡

እንዲያው፡ምናልባት፡

ቢያጠግው፡ቢያደርገው፡

ጊዜ፡መሰንበት፡

ሰው፡አውሬ፡ሆኖ፡ሰውን፡ቢበላው፡

ከየት፡ላይ፡ነው፡ነውሩ፡
ትር፡የሚያሰኘው ?
ሰዎች፡እምቧ፡በሉ፡
ሰብተን፡እንቆይ፡
ጉ ኅንጀ፡ተብለን፡እንዳንሰቃይ፤
እንብላ፡እንጠጣ፡እንሰፋላቸው፡
ጥርሳቸው፡ሲያርፍብን፡
ዱስ፡እንዲላቸው።
እኛ፡የሳልነው፡ጥርስ፡ካልጠረሰ፡በኛ፡
ለኛ፡ዘሮች፡ጦስ፡ነው፡
የሕይወት፡መጋኛ፤
ስለዚህ፡ሰዎቹ፡
እኔ፡እምቧ፡አልኩላቸው፡
ምናልባት፡አጥንቴ፡
መረቅ፡ቢሆናቸው።

ሚያዝያ — ፲፱፻፹፫ ዓ.ም።

## እኔ፡ እንደሚመስለኝ።

እንደ፡ ጆሮ፡ አንቀርም፡
እንደ፡ ቀንድ፡ አንሾርም።
በሻኛ፡ አንገታም፡
እንደ፡ ራስ፡ ሳንታ፡ እንጂ፡
እንደ፡ ሳት፡ አንሆንም።
የወንድ፡ አገር፡ ደዘን፡
ያባቶች፡ ድግ፡ ታጥቀን።
በባሕል፡ ተወረን —
መጥፎ፡ ስም፡ አንግሠን፡
ጥሩ፡ ስም፡ አንተብርም።
አገራችን፡ ለኛ፡ እድለኞች፡ እኛ፡
ታራሚዎች፡ እኛ። ታዳጊዎች፡ እኛ፡
አፍሬዎችም፡ እኛ፡
ከሆንን፡ ከገባን —
አንሆንም፡ መናኛ።
ጉር፡ አንጻሬርም፡

ጨጊካን፡ አንጣስስም፡
እሾህ፡ አንረግጥም፡
ወስን፡ አንገፋም፡
ሥራን፡ ቸል፡ አንልም፡
ማንንም፡ አንቆም፤
ግን፡ ወኔ፡ ጌስማችን፡
ምንጊዜም፡ አይርድም።
እኔ፡ ይመስለኛል፡
እንዲህ፡ ይታየኛል፤
ሰዎች፡ ነን፡ እኅለሁ፡ የሚል፡ እንዴስ፡ ለሌ፡
ሰዎች፡ ነን፡ እሳለሁ፡ እኔ፡ በበኩሌ፤
ማንንም፡ አልመርጥም፡
እከሌ፡ ተከሌ፡
ግና፡ መቼም፡ እንጂ፡
ያልሆነ፡ እንሞር፡ ይሆን፡ ከመሃኅችን፡
ገጼ፡ ብርሃኖቹ፡ ልባዊ፡ ጋኔን፤
አይ፡ እኔ፡ አይመስለኝም፡
እንዲህ፡ አልታየኝም፤
እያየን፡ የማናይ፡ ቀን፡ የተረሳን፡
የጥቁር፡ ጥቁርቁር፡

ዓይናዊ፡ድፍን።

ሉሰኖዴ፡ሉሰሞዴ፡ከመዓጎችን፡
መሞር፡እዱ፡ሆኖ፡
የሚያስጨንቀን።
አይ፡እኔ፡አይመስለኝም፡
እንዲሁ፡አልታየኝም፤
ግን፡ማን፡ማን፡ያውቃል፡
እንሞር፡ይሆናል፤
እንሞር፡ይሆናል፡ጭራ፡ተረፖች፡
ልባዊ፡ሰይጣኖች፡ገጂዊ፡ሰዎች።
እንሞር፡ይሆናል፡
ሥራን፡ቸል፡ባዮች፡
አይሠሩ፡አያሠሬ፡
መንቻካ፡ጨቅጫቃ፡
ስዛቢአ፡መራሬ፤
እንሞር፡ይሆናል፡
የመንበር፡ስስታም፡
ዓይነ፡ሆዳሞች፡
ለጉበዛኜ—ልሳናት፡
እርሽ፡ኩርሽዎች፡

እንኖር ፡ ይሆናል ፡
ካለን ፡ እግዜር ፡ ያውቃል ።
ግን ፡ እኔ ፡ አይመስለኝም ፡
እንዲህ ፡ አልታየኝም ፡
እኔ ፡ እንደሚታየኝ ፡
እንደሚመስለኝ ፡
የለንም ! ካለንም ፡
ዝምብ ፡ እንኳ ፡ እሽ ፡ አንልም ።
እኔ ፡ ይመስሰኛል ፡
እንዲህ ፡ ይታየኛል ።
እኔ ፡ ይመስለኛል ፡ የዲስታ ፡ ፀር ፡
የለንም ! ካለንም ፡ እናወጣም ፡ ፈር ።
እኔ ፡ ይመስለኛል ፡
ብስጭት ፡ መከራ ፡ ፈተና ፡ ችግር ፡
በጭራሽ ፡ የሸሹ ፡ ከኛ ፡ ማፋዲር ።
እኔ ፡ ይመስሰኛል ፡
እኔ ፡ ይመስለኛል ፡ የሥራ ፡ ሰዓት ፡
መዓልትና ፡ ሌሊት ፡ የማንለይበት ።
እኔ ፡ ይመስለኛል ፡
እኔ ፡ ይመስለኛል ፡ አቋራጭ ፡ ያለን ፡

ጥንክር፡ሆነን፡ካደግን፡
ብልህ፡ለመሆን፤
ምን፡ይቸግረናል!

አገር፡እንዴሚ ለው፡እንደሚያወራው፡
ጊሳው፡ሰንበሌጡ፡ሳርና፡ሬሳው፡
ቴጠማው፡ሐረጉ፡ዛፍና፡አበባው፤
አሸዋው፡አረንዛው፡
ሸኮቴው፡ድንጋው፡
ገደል፡ሸንተረሩ፡
ተራራው፡ጉባው
ሸጥ፡ሸለቆው፡ወንዙ፡
ዙሪያችን፡ሚዳው፡
ኮባዜ፡ሬድሞ፡ወራሽ፡ነው፡ያገው፤
ምን፡ይቸግረናል?

ሀብታችን፡ጌጣችን፡
ያገር፡እመቤቱ፡
ኃያል፡አለኝታ፡ናት፡
የመሮር፡ቶርኢቱ፤
ምን፡ይቸግረናል?

ምን፡ይቸግረናል፡ምን፡ይጎድለናል፡

ፗ.ዮ.

የስም፡ቅጽል፡ሆኖ፡
አንቱ፡የሚያስብል፧
ሱፍ፣ሸሚዝ፡ባርኔጣ፡
የውጭ፡አገር፡ባና፡
ሰርቲፊኬት፡ድግሪ፡
ግንብ፡ቤት፡መኪና፣
እስኪ፡የቱ፡የቱ፡የቱ፡ያሻናል፡
የስም፡ቅጽል፡ሆኖ፡
አንቱ፡የሚያስብል፤
ተሽከርካሪ፡ወንበር፡ሺሪ፡ጠረጴዛ፡
ቁስም፡ጎራሽ፡ብዕር፡
ሲጋራ፡መያዣ፣
የቢሮ፡ማሞቴያ፡አየር፡መበረዣ፣
እስኪ፡የቱ፡የቱ፡የቱ፡ያሻናል፡
የስም፡ቅጽል፡ሆኖ፡
አንቱ፡የሚያስብል፧
እኔስ፡ቸግሮኛል፤
እኔስ፡ቸግሮኛል፡የሥልጣኔ፡ጫፍ፡
እሮቅ፡ካይ፡መኖር፡ነው፡
መሬ፡መታቀፍ፣

ወይንስ፡ አፍንጫዬን፡

አየር፡ ላይ፡ መስተል፡

ሹል፡ ጫማ፡ ሰክቶ፡ ልብን፡ መዱሰል ?

ወይንሳ፡ ደግሞ፡

አሚዱ፡ የጠጣች፡

አንገትጌን፡ ገትሮ፡ ሊታሹ፡ መዋል ?

እስቲ፡ የትኛው፡ ነው ?

አበባ፡ ዱረት፡ ላይ፡ ሰክቶ፡ መዞር፡

እውኛ፡ ተጫምቶ፡ ጭሬራ፡ ማዱር፡

ሳያገቡ፡ ፍቺ፡ ኑሮን፡ ማሳፈር፡

እስኪ፡ የትኛው፡ ነው፡

አንቱን፡ የሚያበስር፡—

ክልስ፡ ቋንቋ፡ ይዞ፡

በሰው፡ ላይ፡ መኖር፡

ወይስ፡ ፈልተቶ፡ ዘጋ፡ ሰው፡ ማይናገር፡

እኔስ፡ ቸገሮኛል፡

ትርጉሙ፡ ጠፍቶኛል።

ይህ፡ ነወይ፡ ሥልጣኔ፡

ሥልጣኔ፡ የሚሉት፡

እስከዚህ፡ ነወይ፡

ጥብቅ፡ አሠር፡ አርጉ፡
እንዲሠራ፡ ክደ፤
ደህ፡ ነወደ፡ ደህ፡ ነወደ፡ ሠልጣኔያችን፡
ነፍስ፡ ይማር፡ ዴርቦ፡
ማሳየት፡ ሜጊንታን፡
መጫሚያችን፡ ነወደ፡
ገበና፡ ከታች፡
ወዲየር፡ ሕምጥቆ፡ ሌብን፡ የሚያናች፤
ስሁንስ፡ ጨነቀን፡
መናገር፡ ሕቃተን —
ሕንገት፡ ማወዘወዝ፡ እጅ፡ ማርገብገብ፡
ባይን፡ ቂጥ፡ መማታት፡
ግንባር፡ መሰብሰብ፡
ሕፍ፡ ለጉሞ፡ እንዲከብት፡
መሬትን፡ ማነበብ፡
ቋንቋ ችን፡ ሆኑና፡ ቃሳት፡ ነሬጉን፤
ዋ፡ እንዷያው፡ ሕፍ፡ ለታጅች፡
ሬራሁ፡ እንዲንሆን።
ሠልጣኔ፡ አፍ፡ አውጥቶ፡
ትናገሮ፡ ጨርሶ፡

እኛ፡ዘንድ፡ሲደርስ፡
ዝም፡ሆነ፡ጁርዮ።
አፌር፡መስሎ፡ሠሪ፡
ዲካሚ፡ታታሪ፡
ቅብጥብጥ፡መሠሪ፡
መሆኑን፡ስናውቅ፡
መቀሸር፡መሞሸር፡
ማውራት፡መቀባጠር፡
ሆነ፡እኛን፡ቢንቁ።
ታዲያ፡ምን፡ተሻለ፡
በምን፡ተደለለ?
ጋላ፡አማራ፡ትግሬ፡ኖቱና፡ሱማሌ፡
ወላሞና፡ባሪያ፡እከሌ፡ተከሌ፡
በመባባልና፡አንዱ፡አንዱን፡በማየት፡
ቢሠራ፡እሠራለሁ፡
ቢተኛ፡እተኛለሁ፡እያሉ፡በማውራት።
ወይስ፡በየጎሳ፡ነገር፡በመግመድ፡
አጡዞ፡ጠምዝዞ፡ሰው፡በመሸርደድ።
እንዴት፡ነው፡እንዴት፡ነው፡
የተዳለለው፡

ይኸ፡ሥልጣኔ፡አፉን፡ያሠረው፤
ሮሶሮል፡ነትራኪ፡አላስተምጥ፡ባይ፡
መሆኑን፡እንዲሆን፡

አውቀናል፡ላናይ፤

ታዲያ፡ምን፡ይሻላል፡

እንዲያናግረን፡

የልቡን፡ያንጀቱን፡እንዲያጫውተን፡
ይኸ፡ሥልጣኔ፡የሸረሪት፡ድር፡
ላንቁሶ፡ይመስላል፡

ነገር፡እስኪያዞር፤

ውሉ፡የማይገኝ፡የልስልስ፡ጠንካራ፡
ሽልጥ፡አጭበርባሪ፡ነገረ፡መራራ።
እኔንም፡ገራርቹ፡እያስመረረኝ፡
የገባው፡ልውጣ፡ሲል፡ሲተናነቀኝ፡
ዶሮ፡ማታ፡እያልኩኝ፡ራሴን፡ዱልዬ፡
ኮሶን፡እጋታለሁ፡

ማር፡ማር፡ይላል፡ብዬ፤

ነገር፡ግን፡ስሰማ፡ሰዎች፡ሲናገሩ፡
አሬ፡ነው፡ይላሉ፡

ኮሶ፡አርጊ፡መራኑ።

እጁ፡ነው፡ይሉኛል፡ምርጫ፡ያጠፋው።
አፌ፡ነው፡ይሉኛል፡ቃና፡ያልሰጠው፡
ጥርሴ፡ነው፡ይሉኛል፡ያኅዋዛዉው፡
ሆዴም፡ነው፡ይሉኛል፡ያኅሸራሸው፡
አንጀቴና፡ቆሽቴ፡ማንጠሪያ፡ያጣው፡
ሥልጣኔን፡ሳያልም፡ያወጀለተው።

አዎ፡ወጀለተ፡በሁለንተናዬ፡
ኑሮዬ፡አዲስ፡ሆኖ፡ለሦነት፡ዘዬ።
መልኬ፡ብቻ፡ሳይሆን፤
አእምሮዬ፡ጭምር፡ጥቁር፡ሆነብኝ፡
ለመምሰል፡ኑሮ፡እንኳን፡
መኪያቶና፡ሚስቶ፡እንድሆን፡አሻኝ።

ዱሮ፡ሲናገሩ፡
ያረጀ፡ያፈጀ፡ፍግ፡ይሆናል፡ሲሉ፡
ጨበሬ፡ቆሻሻ፡ጋይም፡ሲያቃጥሉ፡
ይመስለኝ፡ነበረ፡አይጠቀም፡ብልሃት፡
ለካስ፡እንዲያፈራ
ሞራል፡እንዲያኮርት።
እንግዲህ፡ተማርኩኝ፡
እንግዲህ፡ተማርኩኝ፡እማራለሁኝ፡

ሥልጣኔ፡እንዲከፍለኝ፡
የሥልጣኔን፡እፔ፤
ግን፡እንዴት፡ይሆናል፧
ምገኛ፡መታገል፡ምንኛ፡መባት፡
እንደምን፡ብሆን፡ነው፡
የማገኘው፡ሥልቱ፧
ሥልት፡የሥልጣኔ፡
የዱም፡ዋጋ፡ሥጋ፡
የሥልጣኔ፡ሥጋ፡የዱም፡ሥልት፡ዋጋ፤
ጋይ፡ሆኖ፡እየጨሰ፡በሁለንተናዬ፡
ሰዉፍ፡እሳት፡ሆኖ፡
ልቤን፡አያጋዬ፧
እንደ፡አሸን፡ነዛብኝ፡
የዓይን፡ቸጋራም፡
አቧጭቶ፡አመናጭቶ፡
የሚያስክድ፡ወንድም፤
ታዲያ፡ምን፡ይሻላል፡
በምንስ፡ይረታል፤
በምንድን፡ይረታል፡ምንስ፡ይበጃል፡
ለማጥፋት፡ጨርሶ፡

ይኸን፡ያሠረኝን፡

  አጉል፡መጻለል፤

ሰኅኅሻሻለኝ፡

ስኅኅሳዴግኝ፡

ይኸ፡እንካስሳንቲያ—

ለማይጠቅም፡ነገር—

በነጋ፡በጠባ፡ሁልጊዜ፡ሰበካ፡

ይሻላል፡ቢዘጋ፡

  የወሬው፡ፋብሪካ።

ይብቃ፡ይበቃኛል፡አዙረኝ፡እንደ፡

ሥልጣኔ፡አይገታም፡

  እንዲያው፡በለይ፡ለይ።

በሥራ፡ነው፡እንጂ፡

  አድጎ፡ማሸቃነጥ፡

በመምሰል፡አይደለም፡

  አጉል፡በማለጥ።

  እኔ፡ይመስለኛል፡

  እንዲህ፡ይታየኛል።

እኛ፡እኛን፡ፈልገን፡

  ተጋግዘን፡እንሥራ፡

ጅኛ፡ እኛ፤በመሆን፡

ኢንዴ፡ንን ሠራራ።

የካቲት፡ ፲፮—፲፱፻፶፫ ዓ፡ም፡

ሆድ፡የሌለው፡ዓይኗ፡

አጠገቧ፡ሆኜ፡
ሐሳብ፡ይዞኝ፡ሔዶ።
አጠገቧ፡ሆኜ፡
አካሌ፡ተገዶ።
ዓይኗ፡ተሰውጦ፡ባሕር፡ሆኖብኝ፡
እዬሩ፡ቱጭ፡ብዬ፡
ኃዘን፡ጨብጦኝ፡
ወይ፡እራስን፡መርሳት፡
ጨርሶ፡ታማሚ፡
ስወረውርባት፡ጠጠር፡ሰቃቶሚ።
እየዋጠች፡ዝሙ።

የምሞኸ፡ ይባሳል፡
እስኪ፡ ትነግረኝ።
ምነዋ፡ መታኸኝ፡ ያላለቸበትስ።
የምሞኸ፡ ይባሳል፡
እስኪ፡ ትነግረኝ።

ቀሊታም፡ ነው፡ ብሶ፡
ፍቅረ፡ ቢስ፡ ነው፡ ብሶ።
የኔና፡ እሷን፡ ነገር፡
የማያውቅ፡ ሁሉ—
አንዴ፡ ማርያም፡ ጠላት፡
እስኪ፡ የጣድሬኝ ።
እስኪማ፡ ትነግረኝ፡
የምሞኸ፡ ይባሳል፡
ያሳየችበት፡ ይኸንን፡ ውበት፡
አጊጉቶ፡ ዴልሉ፡ መቀመት፡ ሲከት።
የምሞኸ፡ ይባሳል፡—
ቴጠማው፡ ቅንድቧ፡
ሬሳው፡ ሺፋሺፍቷ፡
የሙት፡ ባሕር፡ ከቦ፡
እስኪ፡ ልሰማየቷ።

የምሞሽ፡ይባሳል ፡—

በኔ፡እንዲሾፈብኝ፡ከሩቱ፡ዱሉሉ፡

ያኅየቸበት —

ስንቱን፡ስንቱን፡ቷሟ፡

ሲያስቀር፡ስነኋሉ፡፡

ጉድ፡ሌ ኮ፡እንጂ፡እናንተ —

የኔማ፡የጉዴ፡ነው፡

ሊሰጥም፡ያስተኛል፡

ለዱግም፡ሰክፉ፡

ሁኔታው፡ጨንቆኛል፡፡

ስሄሄ፡እያሰፐ፡

ባሄሄ፡እስቀርቶ፡

እንዶ፡ሳዩ፡ባንዴዜ፡

ሥሮቼን፡ጐቱቶ፡

ካዩኗ፡ወዬ፡እንጓዋ፡

ጉብቶ፡ያልሰረገው፡

የውበቷ፡ውሃ፡ይኸው፡አጥልቶኛል፡

ብወድም፡ባልወድም

እንዲሉ፡ውጦኛል፡፡

ነገር፡ባን፡አለሁኝ፡

መምሬን፡ አውቃለሁ፡
አተነፍሳለሁ።
ልቤ፡ ይሰማኛል፡
ደሜ፡ ይነዝረኛል፣
ዶሬነቀለኛል፣
እንደሳቀሳቀሳቀም፡
እንዲማርገፍገፍም፡
እንዲያ፡ እንዲያም፡ ይለኛል።
ታዲያ፡ ይህ፡ ያም፡ ሆኖ —
በፍጹም፡ በፍጹም፡ አይታወቀኝም፡
ምን፡ እንደማወራም
የት፡ እንደማዘጋም፣
አይታወቀኝም —
እንደምን፡ ሊወቀው —
የሰራ፡ አከሳቴን —
ሆድ፡ የሌለው፡ ዓይኔ፡
ባንዴዬ፡ ሲያሰርገው።
አይታወቀኝም፣
እንደምን፡ ሊወቀው፡
ሆድ፡ የሌለው፡ ዓይኔ —

አዟሪት፡ሆኖ፡ብኝ፡

ድንገት፡ሳላስበው፤

እንደምን፡ልወቀው —

ድንገት፡ሳላስበው፡

ያካኋ፡ሰርግታ፡

ዴሚን፡እየረታ፡

ልቡን፡ሥሩን፡ሰቦ፡እያግተረተረው፤

እንደምን፡ልወቀው፡

ራሱን፡ሳስራው፡

ማጥለቅ፡ማስጨነቁን፡

በደስታ፡ፋና፡እያጥበረበረው፤

ሆድ፡የሴሰው፡ዓይኗ —

ልቤን፡ሥሩን፡ሰቦ፡

አሬ፡ካይ፡ተሰማኝ፡

እግሬ፡ውሃ፡ሆኖ፡

ጨርሶ፡እስኪአደኝ፤

ታዬያ፡ያኸው፡ነወይ፡

ኑሮ፡ያኸው፡ነወይ፡

ሆድ፡በሌሰጡ፡ዓይኗ፡

ቀረሁኞይ፡በቃ፡

ወይ፡ባኘገት፡መቀርቀር፡
ወይ፡የኑሮ፡ሲቃ።

መጋቢት — ፲፱፻፶፯፡ዓ፡ም፡

የወፍ፡ጫጩት፡ወጣት፡

ሬቱ፡እማይኮሰትር፡
ልቡ፡እማያመር።
አሞቱ፡ቀዝቃዛ፡
አካሉ፡ፈዛዛ።
የሥልጣኔ፡እሬሳ፡
የፈረንጅ፡ጥምብ፡አንሳ።
አልሞተም፡ይሉኛል፡
ሞቶ፡እያየሁት፡
ከሴት፡የማይለየው፡
የወንድ፡አብነት።
የውነት፡አስተማሪ፡

ፈንዳንድ፡ተባራሪ።
እንዲሉ፡ምናልባት፡
አባካችሁ፡እስቲ፡ተማሪ፡ልሁን፡
የሚጠቀሰው፡መጣፍ፡
ቢዘልቀው፡ልቤን።
እንዴት፡ነው፡ነገሩ፡
እስኪ፡ይንገረኝ።
እንዴት፡ነው፡ነገሩ፡
የወጣት፡ተግባሩ።
በጥሬ፡ሲያናጋው፡
በጥሬ፡ሲያጣፋው፡
በኩርኩም፡ሲዱቃው፡
በኩርኩም፡ሲተብረው፡
በጉሽም፡ሲያበስለው፡
ሲመዱውተው።
ስድብ፡በማኸሮጉድጉዱ፡
ሲያበሻቀጠው።
መንፈሱን፡ጨርሶ።
ጭራሽ፡ሲገድለው፡
ትምሬያለሁ፡ብሎ፡ዶክተር፡ከሆነ፡

ወንድ፡ ተባይ፡ ሴቱ፡ እንደምን፡ ታመነ፤
የወጣት፡ ልጅ፡ ሥሩ፡
　　　　ካልተጣተረተረ፡
ሲሰድቡት፡ ሲገፉት፡
　　　　ልቡ፡ ካልነፈረ፡
እስኪማ፡ ይንገረኝ፡
　　　　እንደምን፡ ታፈረ፡
ሰው፡ መሆኑን፡ አውቆ፡
　　　　አገር፡ አስከበረ።
ወይንሳ፡ ደግሞ፡ እንደዚህ፡ ዓይነት፡
ነወይ፡ ተረሳጊው፡ ሳገር፡ ሰብነቱ፤
ዓኅማው፡ ሳይ፡ ደርሶ፡
　　　　እሚሠራው፡ ሥራ፡
ሁሉን፡ አጠናቆ፡ በተራ፡ በተራ፡
ማስታወሻ፡ እሚተው፡
　　　　በወንበር፡ አሻራ፤
ነወይ፡ የሚረሳ፡
ደግሞስ፡ የሚባለው፡
ይምጣልኝ፡ ያገር፡ ልጅ፡
　　　　አገር፡ የሚያኮራ፤

ይህን፡ዓይነቱ፡ነወይ

ዶኑር፡የሚባለው፡

ደምጣልኝ፡ያገር፡ልጅ—

በጣሙን፡አዋቂ፡

በጣሙን፡ሥልጡን፡

አንጀቱ፡እያረረ፡

የሚያሳይ፡ጥርሱን።

ይህን፡ዓይነት፡ነወይ፡

ዶሥራ፡የሚባለው፡

ደምጣልኝ፡ያገር፡ልጅ—

በጣም፡ንዴተኛ፡

ልቡ፡የማይተኛ።

ጎልፍ፡ያለው፡እንዴሁ

ዴሙ፡ሲለወጥ፡

ባቦ፡በሥጎሴ፡

ያኘከውን፡ምግብ፡

እንኳ፡የማይውጥ።

ይህን፡ዓይነቶ፡ነወይ፡

ዶዴጎ፡የሚባለው፡

ደምጣልኝ፡ያገር፡ልጅ —
በጣም፡ኃይለኛው፤የሚወጣለት፡
ካቡን፡አንቸፍችሮ፡
ንዴቱ፡ድንገት፤

ኮፍጣናው፡ያገር፡ልጅ፡
እኔ፡መቼ፡አጣሁት፤
ለእንዲህ፡ያለው፡ነገር፡
እንደሌለው፡ስንሬች፤
ካሰራ፡በኋላ —
ወሬ፡አይበሉት፡እንጂ —
እንዴያ፡ከትናዴዱ —
ምን፡እርምጃ፡መሰይክ፤
ብሎ፡እንዲደቀባጥር፡
ድንገት፡ደሜ፡ፈልቶ፡
አረኩበት፡ልክክ፤
ብሎ፡እንዲደቀባጥር —
በቦቅስ፡ባጉነው፤
ከመሬት፡ተሳጋቶ፤
መነሣት፡ሊቃተው፤

ብሎ፡እንዲደቀባጥር፡

ኧጉጢን፡መዝዤ።
ባዛኝቱ፡ማርያም —
አለባልኩት፡ባንዱዜ።
ኀብሎ፡እንዱደቶባጥር፡
የኔ፡ወንድነት።
በሰበሽ፡ሰደዱለም፡
ቦካሴና፡ኮት።
ኀብሎ፡እንዱደቶባጥር፡
ወጊድ፡ነኝ፡
ወንድ፡ነኝ፡
ድሎቶና፡ሹመት፡
መሸለም፡መሸንበት፡
መዝናናት፡መፈራራት።
የማያታልለኝ።
ከዚህ፡በተረፉ፡ግን፡
ሞልቷል፡ያገር፡ልጅ፡
ለችግር፡ብስጭት፡
ለሁሉ፡ኢሚበጅ።
ምንድነው፡ነገሩ፡
ቀላል፡ነው፡ምሥጢሩ፡

የወጣቱን፡ ድካም —
ሥራ፡ ለማወቅ፡
ይቻላል፡ በውነት።
ሌላው፡ ቢቀር፡ እንኳ —
ካካሉ፡ ለማየት፡ ከሥጋው፡ ማሰቱ።
እንጂት፡ አይታይም፡
እስኪዚህ፡ ሲደክም።
አጥንት፡ ጉልጥምቱ —
ፍጹም፡ ተለያይቶ፡
ሎፍሰፍስፍስ፡ ብሎ፡
በቁመናው፡ ሞቶ።
ዘመናይ፡ ደስታ —
ልቡን፡ ወስዶ፡ ሸጦት፡
ቀስ፡ ቀስ፡ እያለ፡
አካሉን፡ አሟሾት።
የዱም፡ ሥሩ፡ ዱርቆ፡
አጥንቱ፡ ተጣብቆ።
መቅኔው፡ በቅልጥሙ፡
መውጫ፡ አጥቶ፡ ተጨንቆ።
እየተነነበት፡

ጓትርትርትር፡አርጉት፡
እንዱ፡አሙሉ፡ቀርቶት፤
እንዴት፡አይታይም፡
እስኪማ፡እስኪ፡እዩት፡
ታገኙበት፡እንዲሁ፡የሰው፡ምልክት።
እኔ፡እንጂ፡አይመስለኝም፡
የዘመኑ፡እድል፤
የዘመኑን፡ወጣት፡
ሰው፡የማያስመስል።
ጭራሽ፡እኮ፡ቀርቷል—
በሥራው፡ሳይ፡ሞቶ፡
በየመዓዘኑ፤
ተብሳልቶ፡ተብሳልቶ።
አፉ፡ከማሰሮ፡አጥንት፡የሚያወጣ፡
ጥርሱ፡ብሽቁጥቅጥቅጥ፡
የሲጃራ፡ጥሳት፡ኩሉ፡የሚያሳጣ፤
ጉንጩ፡ጉጣጉጥ፡
ሥጋ፡ያለው፡ቢያገኝ፡
ሥሩ፡የማያናውጥ፤
ዓይኑ፡በወረንጦ፡የማይለቅም፡

የጓንባሩ፡ሰጕበር —
ያረገው፡ጭልም፤
አንገቱ፡ሰሳሳ፡የሚያዶናግር፡
ፊቸል፡ያሸነፈው —
አልመዘዝ፡ያለ፡
ጠማማ፡ምስማር፤
ዶረቱ፡አንገት፡ሸሸ፡
ውስጥ፡ውስጡን፡የሳተ፡
እንደ፡ሰርዶን፡ሰቃ፡
የተጨራመተ፤
ምኑም፤ ምኑም፡ምኑም፡
ምን፡የማይመስል —
አባካችሁ፡እስኪ፡—
ቁስ፡ቁስ ይበልና፡
ያስሳው፡እራሱን፤
ዶሞ፡ሰው፡ነኝ፡ብሎ፡
በከንቱ፡ውዱሴ፡እንዱይታሰል።
ጉድማ፡እንጃ፡እናንተ፡
ሰው፡የማያዶናግር፤
በመጣቱ፡ሳያውቅ፡የዶረሰው፡ታምር።

ምን፡ይሆን፡ውጤቱ፡ያብተከተከው፡
የውስጡን፡የውስጡን፡
የውስጡን፡በሳቦት፡
የሚያስጨርሰው፤
ነቀዝ፡ነወይ፡ኑሮ፡
ተምች፡ነወይ፡ኑሮ፡
አንጓ፡አንጓውን፡ግጦ፡
አካሉን፡አከስሮ፡
መሬት፡የሚያስመስል፡
የሚዷፋ፡አዙሮ፤
እልቅልቅ፡ነወይ፡
ስልስልስል፡ነወይ፡
ሙትትት፡ነወይ፡
ያስጊዜው፡ዱርስ፡
ተምሮ፡ተምሮ፡
ዕውቀት፡ተንተርሶ፤
ሔዬ፡ያልኝ፡መሠልጠን፡
ሔዬ፡ያልኝ፡መግፋት፡
ሔዬ፡ያልኝ፡መታወቅ፡
ሔዬ፡ያልኝ፡መሳቅ፡

እንዴት፡ያለው፡ኑሮ —
ሰው፡የሚያራቶቱ።
እራስ፡በራስ፡ሰልሮ —
ከሰውነት፡መዝገብ፡
ከኑሮ፡ተገሮ —
እንቆቅልሽ፡ማኅበዛቱ።
ሞት፡ሞትን፡ቢሰርቱ።
የጭንቅላቱ፡ደም፡
የጭንቅላቱ፡ሰም፡
በውሃ፡ተጠርጎ።
ኮረኮንች፡ድንጋዩ፡
ያለማል፡በሚባል፡
በፍጣፍጣ፡ታሽጎ።
እንዴ ያበቀል፡ነወይ —
ሰው፡የሚነዝረው፡
ሰው፡የሚሬራው፡
እሬቱ፡ሳይ፡ሲሆን፡
አዴጣ፡አዴጣ፡ብሎ፡
ትማር፡ትማር፡ብሎ፡
ካጠገቡ፡ሊሔድ —

ቱቀጠፉ፡ተቀጠፉ —
ድረቁ፣ ድረቁ፣ ድረቁ —
ድርቅርቅርቅ፡በሉ፡
ካሉ፡እማያስኘው፤

እንዲፋችሁ፡ይሆን፡
እንዲሳችሁ፡ይሆን፡
ዱሮም፡ጤውት፡ነውና፡
ይድረቅሳችሁ፡

ማፋጊያ፡ከሆነ፡ለማያፈራችሁ፤
መቼስ፡ምን፡ይደረግ፡—
በዚያም፡በዚህ፡ካለህ —
የወፍ፡ጫጩት፡መጣት፡
ካታተህ፡ለመሳት፤

መለቆር፡እንዲጎመስ፡
ከናት፡ወፍ፡ለመጉረስ፡—
ዱግሬ፡ተንተርሰህ —
ወዱ፡ሳይ፡እንጋጠህ፡
ቆብ፡ለፍክን፡አነታንት —
ይመስልህ፡እንዲሆን፡
መኖ፡አፍህ፡የማይወድት።

ጥቅምት፡ ፩ ፲፱፻፶፯ ዓ.ም.

እማዬ፡ እየለሌ።

ባልሽ፡ ጐበዝ፡ ተጋዥ፡
ታታሪ፡ ገበሬ።
አርሶ፡ የሚያገባ፡
በትንፏሼ፡ በሬ።
አንቺ፡ ባለሞያ፡
የጐፏሽ መታያ።
እንጀራሽ፡ ዓይናማ፡
ሰው፡ የማያሳማ።
ወጥሽ፡ ኩርጥ፡ ያለ፡
ጠላሽ፡ አንዴ፡ በቃኝ፡
ከዚህ፡ የበለጠ፡
ሰው፡ ምን፡ ሲያገኝ፡ ይመኝ ?
ተመስገን፡ ነው፡ እንጂ፡
ሽለሌ፡ ሽለሌ።
እማዬ፡ ምን፡ ይኳል።
መቼስ፡ እያለሌ።

ነሐሴ — ፲፱፻፶፯ ዓ ፡ ም ፡

## አይመረመሬ ፡

አይመረመሬ ፡
ዋማ ፡ አገረ ፡ ሩቱ ፧
ሰናቴን ፡ ሬዋርቆ ፡
እንጁየር ፡ አስሎቶ ፡
ሐልም ፡ መሳይ ፡ ቀሬቴ ፡
የሴሌቶ ፡ አሢሬቴ ፡
የሠራ ፡ አከሳቴን ፧
ድንገት ፡ ኅሳስበው ፡
ቢያተረማምሰው ፧
አወጣው ፡ ኅትቾ ፡
አወጣው ፡ ድቀቴን ፡
አወጣው ፡ ኖፍቆቴን ፡
ያሰውን ፡ ተኛቾ ፧
አንዲማርግ ፍገፍም ፡
አገዩመሳወከም ፡
ውስጥ ፡ ውስጢን ፡ ተሰማኝ ፡

ቀዝቀዝቀዝም፡አለኝ።

ዱብለውና፡አልሁ፡

ሌቤ፡ኖሮ፡ኖሮ፡

ፏ፡ብሎ፡በድንገት፡ተተራመሰብኝ፡

እንዲያ፡እንዲያ፡እንዲያም፡አለኝ።

ብቻ፡እንጃ፡ወንድሜ፡

መቸም፡አለው፡ነገር፡

ሔቱ፡ሔቱ፡

ስቀ፡ስቀ፡

እንክትክት፡ስብርብር፡

ክርሽምሽም፡ለሚያደርግ፡

ለእንዲህ፡ያለ፡ታምር።

ሲነሣ፡ተሰማኝ፡

ከቁርጭምጭሚቴ፡

ሲወርድ፡ተሰማኝ፡

ከራሴ፡ካናቴ።

ሲደርስ፡ተሰማኝ፡

እንደቀጭን፡አየር፡

ሲርርርርር፡

ወጹደሞቹ፡አስሉቹ፡

ያይኔን፡ዙሪያ፡ገደል፡
ሲደግዝ፡ተንሠራፍቶ፡
ተሰማኝ፡በድንገት፡
ዙሪያው፡ሲዱምን፡
አሱ፡እንኳ፡ባሕሩ፡
አረሎዮት፡ወጥኝ፤
አቆረዘዘብኝ፡
አልገታም፡አለኝ፤
ያንዱን፡ዓይኔን፡ጥጥኩኝ፡
የሊሳው፡አታተኝ፤
ጠብ፡ሐለ፡በድንገት፡
አኳ፡ያለችበት፤
በእንባዬ፡ጠብታ፡ሕየኋት፡ድንገት፡
አወደ፡ሕልማምለጥ፡
ወደ፡ዴካማነት፤
ትርምስምስምስምስምስ፡
አሰብኝ፡ሕንጀቴ፡
ሽብርብርብርብርብር
መካው፡ሊካካቴ፤
ጨነቀኝ፡ጠበበኝ፡

እንዴት፤ እንዴት፡ልርሳት፡

እንዴምን፡አባቴ።

ትቻት፡ትቻት፡ቀርታ፡

ልቤን፡ሠርዠ፡ብዬው፡

በተእዛዝ፡አቁሜው፤

ትቻት፡ትቻት፡ቀርታ፡

ዓይኔን፡እንዴሳያት፡

እንዴሳያት፡ዓይነት፡

ለዟረት፡አርጌው፡

በሌሎች፡ይልየው፤

ትቻት፡ትቻት፡ቀርታ፡

ሐሳቤን፡ኑሮዬን፤

በዙረት፡ወስኜው፡

እንዴምን፡ወዴሳይ፡

መጠቀች፡ዴንገት —

በውሃ፡ተሞና —

ባዶኑ፡ለመውጣት።

እንዴምን፡ተነነ፡

ምኘስ፡ኤከነሣው፡

ረጋቶ፡የነበር— ልቤ፡ያስቀረው።

ምክኑ፡ችግሽ፡ነወደ፡
ዘሎ፡ለመውጣት፡
ከልቤ፡ኅንጀቴ፡ያስተሳሰፍኩት፤
ታዲያ፡ምኑን፡በጀኝ፡
ምኑን፡ለመንኩት፡
አንጀቴን፡የውስጤን—
የኔን፡አካሳት፤
ምሥጢሬ፡በሙሉ፡
እንዲሁ፡እንዲሆኑ፡
በማያወላውል—
በአእምሮ፡ካሜራ፡
ፎቶው፡ከተሠራ፤
እንዲሁ፡እንዲሆኑ፡
የተነሣው፡ፎቶ—
አንጀቴ፡በገባው—
ባንድ፡ዓይን፡ውሃ፡ርሶ፡
ውኍ፡በፈለቀው፡
በጠብታ፡እንባዬ፡
ምስሉ፡ታጥቦ፡ደርሶ፡
ድንገት፡ተከሠቶ፡ከተርበተበትሁ፡

የቱ፡ ሳይ፡ ነው፡ ጥናቱ፡
እንዴትስ፡ እሰሁ፧

ብቻ፡ እንጂ፡ ወንድሜ —
መቼም፡ ዕለው፡ ፈርፈር፡
ለነገር፡ መነሻ፡ ለመነሻ፡ ነገር፤
በእንግዩ፡ ጠብታ፡ ታየኝ፡ በድንገቱ፡
ያ፡ መጫወቻችን፡
ያሻንጉሊት፡ ቤት፤
ያ፡ የምንሠራው፡
ያ፡ የጭቃ፡ በሬ፡
ያ፡ የጭቃ፡ ቦምብ፡
ከሷ፡ ጋር፡ ሆነና—አገኘቸ፡ ሰበብ፧
ታየኝ፡ ያ፡ ጨዋታ፡
ያ፡ የምጓደ፡ ካባችን፡
የምጓደ፡ ሰድጂችን፡
ዱብብቆሻችን፡
ሽክክሞሻችን፡
ባልልቦሻችን፡
ቅልልቦሻችን፡
ያገዷዎች፡ ዝናር —

ከመታ፡አሜሠራው —
ኢሳማ፡መምቻችን፤
ታየኝ፡ያ፡ጨዋታ፡
እንዲያ፡መሳቲያችን፡
ሬቱን፡አብስለን —
ከመሬት፡በመምታት፡
ሰው፡ማስደንገጫችን፤
ታየኝ፡ያ፡ጨዋታ፡
የገደል፡ማሚቶ፡
ዱሮ፡ልስጥሽ፡ዱሮ፡
ያ፡እሰዴ፡ሰዴ፡ጨዋታ፡
የማታ፡የማታ፤
ታየኝ፡እንዲህ፡ድንገት —
ድንገት፡ሳሳስብ፡
ከኋ፡ጋር፡ሆነና፡ልጓኝቶ፡ሰበብ፤
ብቻ፡እንጂ፡ወንድሜ —
መቼም፡አለው፡ነገር —
አለው የዱሮውስ
አንዲህ የማጊጊት
እንባ፡የማስመጣት፤

## ስሜት ፡ የመቀስቀስ፤

ኢለው ፡ የዱሮውስ ፡
ብዙ ፡ እማይረሳ —
አሰው ፡ የዱሮውስ ፡
የዛሬን ፡ መሳዩ —
ፍቅራችን ፡ ለአሳሳ ፡
ብዙ ፡ እማያገሳ።
ቀልዷና ፡ ጨዋታው ፡
ከጅ ፡ የሚጀምረው።
የጣት ፡ ጨዋታችን ፡
የሚያጓዩረዱረው ፡
እኔ ፡ ቀዩምኩ ፡ ብሎ —
ዱሶ ፡ እሚጀምረው።
ከመዱፍ ፡ ሥር ፡ ይዞ ፡
ቀለ ፡ ብሎ ፡ ተጉዞ።
ብብትን ፡ ሳይነካ ፡
ጊጉቶ ፡ የሚቀረው።
ጓፋም ፡ ቢል ፡ ብብትን ፡
ዱፍሮ ፡ የማያልፈው ፡
ታየኝ ፡ ያ ፡ ጨዋታ ፡

የጨርቃ ፡ ትዝታ ፤
ቋ፡ ክም ክም ክም ክም ክም ፡
ክም ክም ፡ የማያዩርገው ፤
በጣም ፡ ቸነገ ፡ ሲል ፡
የሚያስተቃትረው ፡
ትንፋሽ ፡ አሳጥሮ —
ያስመነጋገር ፤ ያስመንተሳተስ —
እያስተፋፈረ —
ሳይታወቅ ፡ ጊዜ ፡ አሳስሮ ፡ እሚተወው ፤
ዋ ፡ እኔን ፡ እንዲህ ፡ ሲሆን ፡
ነበር ፡ ብዙ ፡ ነገር —
በጨትሳ ፡ አንጓሳቸን ፡
ትርጉሙን ፡ ያልያዝነው ፡
ምክኑ ፡ ያልታወቀው ፤
በእንባዬ ፡ ጠብታ —
ዋ ፡ ጉድ ፡ መስንበት ፤
ትርፎ ፡ ምሮ ፡ ሰካ —
ሞሮ ፡ ሞሮ ፡ ሞሮ ፡
ያልታሰበ ፡ ነገር ፡ ያሳንዱች ፡ ቀጠሮ ፡
ድንገት ፡ ከተፍ ፡ ብሎ —

ታየኝ፡በድንገት፡
ታየኝ፡ፎልፏሳው፡
ታየኝ፡ወሳሳው፡
የሚያዩኖግረው፡
እንዷንዱ፡ግፋ፡ሲል፡
አንዷንዱ፡በድንገት፡
መምጫው፡ሳይታወቅ፡
በገባ፡እሚያሳርገው።

በእንባዬ፡ጠብታ፡
ታየኝ፡ያለፈው፡
የምትሮጥበት፡ሰንበሌጥ፡ሬሳው።
ራሷ፡እምታስረው፡ስንብጡ፡ቴጠማ፡
የምትሮጥበት፡ጭው፡ያለው፡ፋልማ።
ታየኝ፡በየፈርጁ፡ያ፡ያ፡የዱሮው፡
የዱሮው፡የዱሮው፡
ዱሮው፡የዱሮው፡

የነበረው፡ሁሉ፡
እኔን፡ጭምር፡ትምርት፡
ዕውቀት፡ያልገባው።
በእንባዬ፡ጠብታ፡ታየኝ፡በድንገቱ፡

የምታፌትሬቸው፡እነዚያ፡ሁለቱ፤
እሷ፡እንዴስረዷችኝ፡
ባልና፡ሚስቴቱ፡
ባሏ፡የሞተ፡እንደሁ፡የምትሰደደው፡
ሚስቴቱ፡ብትሞት፡ያ፡የሚሰደደው፡
ታዩኝ፡ሁለቶቹ፡ሶረኔት፡ሶረኔው፤
ትዝ፡አለኝ፡በድንገት፡

ያ፡የምታዜመው፡

የደጋ፡ሶረኔ፡
የቆላ፡ሶረኔ፡
ነዩ፡እንኮር፡ከኔ፡

እያለች፡ሁልጊዜ፡የምትደጋገመው።
ዋማ፡ያጋጣሚ፡የትንቢት፡መናገር፡
እሷና፡እኔም፡እንደያ — እንደሀ፡
ሆነን፡ልንተር።